# አዲስ ዘመን

እፕድ

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 174 የካቲት 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፡- በረከት ታደሰ

## “የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን ኅብረት ገንኖ ከእኔነት ይልቅ እኛነት ተጋምደው የታየበት ዓውድ ነው”

- አቶ አገኘሁ ተሻገር
የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

ገጽ5

# መከላከያ ሠራዊት እንደ ዓድዋ ጀግኖች የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማስከበሩን ይቀጥላል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- መከላከያ ሠራዊት በሁሉም መስክ እየዘመነ ግዳጁን በብቃት በመወጣት እንደ ዓድዋ ጀግኖች የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማስከበሩን እንደሚቀጥል የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ። 128ኛው የዓድዋ ድል በዓል በድምቀት ተከብሯል።

የኢፌዴሪ የመከላከያ ሠራዊት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በዘመናዊ ትጥቅ ተደራጅቶ ባሕር ተሻግሮ የወረራትን የፋሺዝም ኃይል ድል ያደረገችው በሕዝቦቿ አንድነት ነው። ዓድዋ ለእኛ የአንድነታችን፣ የጥንካሬያችን እና የአሸናፊነታችን ተምሳሌት ነው። መከላከያ ሠራዊትም በሁሉም መስክ እየዘመነ ግዳጁን በብቃት በመወጣት እንደ ዓድዋ ጀግኖች የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማስከበሩን ይቀጥላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወኔ፣ በጀግንነትና በፅናት ተዋግቶ ወራሪን በማሸነፍ አንፀባራቂ ድል አስመዝግቧል። ድሉ ቅኝ ገዢዎችን ክፉኛ አስደንግጧል ያሉት ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ፤ ነገር ግን ድሉ ትልቅነቱን የሚመጥን ዋጋ ሳይሰጠው በየዓመቱ ለትውስታ ብቻ እየተከበረ ቆይቷል ብለዋል።

የአሁኑ ትውልድ ያማረ እና ታሪኩን በተሟላ ሁኔታ የሚዘክር የድል መታሰቢያ መገንባቱን ጠቅሰው፤ በአዲስ አበባ የተገነባውና የዓድዋን ድል በልኩ የሚዘክረው መታሰቢያ ለመላው ኢትዮጵያውያን፣ ለአፍሪካውያንና ለጥቁር ሕዝቦች ኩራት ሆኖ መቆሙን ተናግረዋል።

መከላከያ ሠራዊት..ወደ ገጽ 5 ዞሯል

ፎቶ፡- በረከት ታደሰ



የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

## የዓድዋ ድል በመላው ኢትዮጵያውያን ተሳትፎና ተጋድሎ የተገኘ አስተሳሳሪ ድል ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፤ የዓድዋ ድል በመላው ኢትዮጵያውያን ተሳትፎና ተጋድሎ የተገኘ አስተሳሳሪ ድል ነው ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት 128ኛውን የዓድዋ ድል በዓልን በማስመልከት ትናንት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፏል፡፡

የዓድዋ ድል በመላው...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## ‹‹የአምራች ዘርፉን በማስፋፋት ሀገርን መስወጥ ካልተቻለ አባቶቻችን የሰጡን ነፃነት ቀጣይነት አይኖረውም››

-አቶ መላኩ አለበል
የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ገጽ5
















ዜና

# ቅድመ አያቶቻችን ነፃ ሀገር እንዳስረከቡን ለቀጣዩ ትውልድ ገናና ኢትዮጵያን ማስረከብ ይኖርብናል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ጀግኞች ነፃ ሀገር እንዳስረከቡን ለቀጣዩ ትውልድ የበለፀገች፣ ሠላሟ የተጠበቀ፣ ዲሞክራሲያዊትና ገናና የሆነች ኢትዮጵያን ማስረከብ ይጠበቅብናል ሲሉ የዓድዋ ድል በዓል ተሳታፊዎች ተናገሩ። የ128ተኛው የዓድዋ ድል በዓል “ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ድል!” በሚል መሪ ቃል ትናንት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በድምቀት ተከብሯል።


ካሰች ዋጋሪ አዶ


አቶ ተፈሪ ቢያዝን


ወይዘሮ ካሠች አየለ

የበዓሉ ተሳታፊ ካሠች ዋጋሪ አዶ ለኢፕድ እንደተናገረችው፤ የዓድዋ ድል የኅብረ ብሔራዊ አንድነት መገለጫ፤ የጥቁር ሕዝቦች ከፍታም ጭምር ነው። ቅድመ አያቶቻችን ከዛሬ 128 ዓመታት በፊት የጣሊያንን ወራሪ ሠራዊት ዓድዋ ላይ በብሔራዊ የአርበኝነት ስሜት የማይቻል የሚመስለውን አንፀባራቂ ድል ተቀዳጅተዋል።

ይህም ድል ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ችቦ እና ዓርማ በመሆን ከአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ነፃ እንዲወጡ አስችሏቸዋል ያለችው ካሠች ዋጋሪ፤ ከዓድዋ የወረስነው መንፈስ አሸናፊነትን፣ በኅብረብሔራዊ አንድነት፣ አብሮ መቆምን፣ በችግሮች ያለመንበርከክና ፅናትን ነው ብላለች።

እኛ የዛሬ ትውልዶች በየተሠማራንበት ሙያ ሀገራችንንና ሕዝቦቿን የሚያኮሩና የሚያለሙ ተግባራትን በኅብረ ብሔራዊነትና በወኔ በመተግበር ለቀጣዩ ትውልድ የበለፀገች፣ ሰላሟ የተጠበቀ፣ ዲሞክራሲያዊትና ገናና የሆነች ኢትዮጵያን ማስረከብ ይጠበቅብናል ስትል ተናግራለች።

የበዓሉ ተሳታፊ ወይዘሮ ካሰች አየለ በበኩላቸው፤ የዓድዋ ድል በዓል የራሱ የሆነ ቋሚ ጉልህ መታሰቢያ ያልነበረው ቢሆንም ዘንድሮ ለድሉ የሚመጥን የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በመገንባት 128ኛውን የዓድዋ ድል በዓል “ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ድል!” በሚል መሪ ቃል በልዩ ሁነትና ድምቀት አክብረነዋል።

ይህ ግዙፍ መታሰቢያ አዲሱ ትውልድ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ላለው አሰባሳቢ ታሪክ ያለውን የላቀ ከብር የሚያሳይበት፣ በዘመኑ ተሻጋሪ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ ያኖረው ታላቅ አሻራው ነው ያሉት ወይዘሮ ካሠች፤ ይህም ትውልዱ በዓድዋ እሴቶች እየታነፀ ታሪኩን ጠብቆ፤ ሀገርን አጽንቶ የማዝለቅ ታሪካዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን አመላካች ነው ብለዋል።

በዓድዋ ድል በዓል መኩራት ብቻውን በቂ አይደለም። ነፃነታችንን ማስከበራችን ጥሩ ነገር ሆኖ ሀገራችን እስካልበለፀገች ድረስ ነፃነታችን በቂ አይደለም። የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ነፃነታችንን በብልፅግና ማረጋገጥ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በቀጣናው ሠላምና ደህንነትን በማረጋገጥ እና ሽብርተኝነትን በመዋጋት፣ ያልተገቡ ውጭ ጣልቃ ገብነቶችን እምቢኝ በማለት፣ ሠላም በማስከበርና ሌሎች ፓን አፍሪካኒዝም ማዕከል ያደረጉ በርካታ አኩሪ ሥራዎች ተከናውነዋል ያሉት ደግሞ የበዓሉ ተሳታፊ አቶ ተፈሪ ቢያዝን ናቸው።

ባለፉት ዓመታት የእኛም ትውልድ እንደ ቀደምት አባቶቹ በርካታ የልማት ሥራዎችን እየሠራ ተስፋ ፈንጣቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል። በሀገራችን እየተገነቡ የሚገኙ የዓባይ ግድብና ሌሎችም ትላልቅ ፕሮጀክቶች በስኬት አብነት የሚጠቀሱ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲሁም ሀገራችን በቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለምቀፋዊ መድረኮች ያላትን ተሰሚነት ከፍ ለማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነት አለብን ያሉት አቶ ተፈሪ፤ ለመጪው ትውልድ የበለጸገች ሀገር ለማስረከብ እንዲተጋ በአደራ ጭምር ለማሳሰብ እወዳለሁ ብለዋል።



አቶ አማረ ታረቀኝ

# ባለሥልጣኑ አሽከርካሪዎች በእግረኛ መንገድ ላይ መኪና ከማቆም እንዲቆጠቡ አሳሰበ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን አሽከርካሪዎች በእግረኛ መንገድ ላይ መኪና ከማቆም እንዲቆጠቡ አሳሰበ።

የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አማረ ታረቀኝ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በእግረኛ መንገድ ላይ ተሽከርካሪዎችን ማቆም መጥፎ እና ሕገወጥ ተግባር ነው። በእግረኛ መንገድ ላይ መኪና ማቆም እግረኞች በመኪና መንገድ ላይ እንዲራመዱ ያስገድዳቸዋል።

በተለይም የትራፊክ መጨናነቅ ባለባቸው አካባቢዎች የአደጋ ስጋትን ይጨምራል። እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት ይሆናል ያሉት አቶ አማረ፤ አሽከርካሪዎች በእግረኛ መንገድ ላይ መኪና ከማቆም ሊቆጠቡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ለአሽከርካሪዎች ስለጥሰቱ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና ያለቅጣት ተገዢ እንዲሆኑ እድል ለመስጠት እየተሞከረ ነው። ነገር ግን ማስጠንቀቂያዎች ሳይሰሙ ሲቀሩ ጥብቅ እርምጃዎችን ይወሰዳሉ ያሉት አቶ አማረ፤ ይህም በደንብ ቁጥር 393/2009 መሠረት ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በእግረኛ መንገድ ላይ ተሽከርካሪዎችን የማቆም ተግባር በእግረኛ መንገድና በሰዎች ደህንነት ላይ በሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ አማረ፤ ባለሥልጣኑ የመኪና ማቆሚያ ደንቦችን ለማስከበር እና የእግረኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚሠራውን ሥራ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

እንደ አቶ አማረ ገለፃ፤ በእግረኛ መንገድ ላይ መኪና ማቆም የእግረኛ መንገዱ እንዲቆፈር እና እንዲበላሽ ያደርጋል። ይህም የከተማዋን ውበት ያበላሻል። የገንዘብ፣ የጉልበትና የጊዜ ኪሳራም ያመጣል። በተጨማሪም የትራፊክ ፍሰትን በማስተጓጎል መጨናነቅን ይፈጥራል። የእግረኛ መንገዶች ለእግረኞች የተዘጋጁ ናቸው።

የከተማዋ ነዋሪዎች በእግረኛ መንገድ ላይ የቆሙ ተሽከርካሪዎች ሲያጋጥማቸው የመኪና ማቆሚያ ደንቦችን የማስከበር እና የሕዝብ ቦታዎችን ደህንነት እና ተደራሽነት የማረጋገጥ ሥልጣን ላላቸው የሕግ አስከባሪ አካላት ጥቆማ እንዲያደርጉም መክረዋል።

# “ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን የአንድነትና የፅናት ምሳሌ ነው”

## -የሃይማኖት አባቶች

ታደሠ ብናልፈው

የአዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል ለመላ ጥቁር ሕዝቦች ነፃነት ያቀዳጀና ለኢትዮጵያውያን ደግሞ የአንድነትና የፅናት ማሳያ ምልክት ነው ሲሉ የሃይማኖት አባቶች ገለጹ።


አባ መላከገነት ዘማሪያም

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የፉሪ ፀርሀ ቅድስት ሀና ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ አባ መላከገነት ዘማሪያም ሙጨ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል ለጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ፈርጥ ነው።ለኢትዮጵያውያን ደግሞ፣ የአንድነትና የፅናት ማሳያ ምልክት ነው። ከዚህ መነሻነትም በዓሉን በአንድነት በሰላምና በፍቅር ልናከ ብረው ይገባል፡፡

ዓድዋ ሁሉንም የሚያስተምር፤ ትናንትን ከዛሬ ዛሬንም ከነገ የሚያስተሳስር የአንድነትና የጽናት ምሳሌ የሆነ በዓል ነው ብለዋል፡፡


አሊ ኡማር ሙሐመድ

የድል መታሰቢያ በዓሉን ሀገርና ቤተክርስቲያን በጋራ የሚያከብሩት ነው ያሉት አባ መላከገነት ዘማሪያም፤ ድሉን በሀገራዊ እድገት ለመድገም ወጣቱ ጠንክሮ መሥራት እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

የመላ ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል እና ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ የአንድነትና የፅናት ዓርማ የሆነውን የዓድዋ የድል በዓል የሃይማኖትና የፖለቲካ አስተሳሰብ ሳይቀላቀልበት፤ የተሳሳቱ ትርክቶችን በማረም ለትውልድ ለማሻገር በትኩረት መሥራት ይገባልም ሲሉ ተናግረዋል፡፡


ፓስተር ሙሉጌታ ሥዩም

የሃይማኖት አባቶችና የሀገር መሪዎች ሕዝባቸውን በቅንነት በማገልገል ዘላቂ ልማትናሠላም ለማምጣት ዳግም የዓድዋን ታሪክ መሥራት አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የመስጅድ አስተዳዳሪ የሆኑት አሊ ኡማር ሙሐመድ በበኩላቸው፤ የዓድዋ የድል በዓል ለዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ፈርጥ፤ ለኢትዮጵያውያን የአንድነት ሰንሰለት ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያዊ አንድነት እስከ አፍንጫው የታጠቀን የጠላት ኃይል በኋላቀር የጦር መሣሪያ የሰባበረ፤ የሀፍረት ካባ ያለበሰ ትልቅ ኃይል ነው፤ ይህን አንድነት በማጠናከር ሀገርን ለማሳደግና ሠላምን ለማስፈን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያዊነት በደም፣ በሥጋና በአጥንት የተሳሰረ በመሆኑ የአንድ ሀገር ሕዝብ ከአድማስ አድማስ ተነስቶ ዓድዋን የመሰለ ታላቅ ድልን መቀናጀት ችሏል፤ ወጣቱም ከዚህ ታሪክ ተምሮ በሀገሩ ላይ ዘመኑ የሚጠይቀውን አሻራ ለማሳረፍ መሥራት አለበት ሲሉ አመልክተዋል።

በዓድዋ ዘረኝነት፤ ልዩነት፤ መገፋፋትና መጠላለፍ ሳይኖር በኅብረ ብሔራዊነት ታላቅ ድል ማስመዝገብ ተችሏል ያሉት ደግሞ ፓስተር ሙሉጌታ ሥ ዩም ናቸው፡፡

ፓስተር ሙሉጌታ እንዳሉት ዓድዋ ለመላ ጥቁር ሕዝቦች ነፃነትን ያቀናጀ ድል ነው፤ ለኢትዮጵያውያን የአንድነትና የፅናት ውብ ቀለም ነው፤ በመሆኑም በፍቅርና በአንድነት ልናከብረው ይገባል፡፡

ወጣቱ ትውልድም በኅብረ ብሔራዊ አንድነት ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ጠንክሮ መሥራት ይኖርበታል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓድዋ የኅብረ ብሔራዊ-አንድነት ዓርማ!

ዓድዋ ኢትዮጵያውያን ለአንድ ሀሳብና ዓላማ ሲሰባሰቡ ጠንካራ የማስተባበር፤ የመምራት፤ የመደማመጥና ፈተናዎችን በአብሮነት የመሻገር ችሎታ እንዳላቸው ያስመሰከሩበት ታላቅ የድል ታሪክ ነው። ለኢትዮጵያውያን የአርበኝነት ዓምድ፤ በእሳት ተፈትኖ የነጠረ፣ በወጀብ የማይናወጥ፣ ኅብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት የተገለጠበት እና የታነፀበት የብሔራዊ አርበኝነት ምሰሶ ነው ።

የኢትዮጵያውያን አይበገሬነት፤ ጀግንነት፣ ኅብረትና አንድነት በተግባር የተመሰከረበት፤ የብሔራዊነት ምልክት፣ የወል ታሪካችን ዓርማ ነው። ኢትዮጵያውያን ከጫፍ ጫፍ በወል ተምመው ያስመዘገቡት፤ የጋራ ትናንትን ከነገ ጋር ማስተሳሰሪያ ገመዳቸው ነው። ዛሬን ቀና ብለው መሄድ ያስቻላቸው የአባቶቻቸው የአርበኝነት የተጋድሎ የድል ታሪክ ነው።

ዓድዋ ብዝኃነትን ያከበረ፣ አብሮነት ለሁለንተናዊ ድል ወሳኝ መሆኑን የሚያሳይ ለኢትዮጵያ ክብርና የግዛት አንድነት በተከፈለ የጋራ መስዋዕትነት የተገኘ የኢትዮጵያውያን የወል ድል ነው። ኢትዮጵያ በሁሉም መስክ በተሰናሰነ የብሔር-ብሔረሰቦች ላብ እና ደም ድምር ውጤት የተገነባችና በወል ጥረቶቻቸው የምትበለጽግ ሀገር መሆኗን ከዚህ የበለጠ ማሳያ የለም።

ኢትዮጵያውያን ከወል ትርክት ይልቅ የተናጠል ትርክቶችን በማጉላታችን አንዳችን ከአንዳችን አላስፈላጊ ግጭቶችንና ጦርነቶችን በማድረግ ተገቢ ያልሆነ መስዋዕትነት መክፈላችን እና አገራችንን ከሥልጣኔ ማማ አውርደን የድህነት ማጣቀሻ ማድረጋችን የማይታበል ሐቅ ነው።

ኅብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን ለማጠናከር፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ማበብና አጠቃላይ ሀገራዊ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት ይመጣ ዘንድ ከተቃርኖ ትርክት በመላቀቅ ገዥ ብሔራዊ ትርክትን በማጽናት ሀገራዊ መግባባትን ለማዳበር ፀንተን በጋራ መቆም አለብን። በሀገራችን የቂምና የጥላቻ ታሪክ ምዕራፍ እንዲዘጋና በብሔራዊ አርበኝነት የተገነባ ብዝኃነትን ያማከለ አካታች የፖለቲካ ሥርዓት ይኖር ዘንድ ትውልዱን ከዓድዋ የተሻለ ሊያስተምረው የሚችል ነገር የለም።

እንደ ዓድዋ ድል ሁሉ ኢትዮጵያን ወደ ላቀ ከፍታ ለመውሰድና ታሪኳንና ክብሯን የሚመጥን ሁለንተናዊ ከፍታ ለማብሰር የሁሉንም ኢትዮጵያውያን የጋራ አስተዋፅዖ ይጠይቃል፡፡ እናም ዘመን ተሻጋሪና አካታች የሆነ ብሔራዊ ገዥ ትርክት በመገንባት ለትውልድ ማውረስ ይገባናል።

የዓድዋ ድል ስኬታማ የሆነው በመላው ኢትዮጵያውያን የተደመረ የአንድነት መንፈስ በመሆኑ አሁንም ሆነ ወደፊት የሀገራችንን እድገትና ብልጽግና የምናረጋግጠው አሰባሳቢ በሆነ ብሔራዊ ገዥ ትርክት የወል እውነቶቻችንን እያፀናን በአብሮነታችን መፅናት ስንችል ነው። ለዚህም የዓድዋ ድል ውጤት መነሻ የዘመቻው መሪዎች፣ ዘማቾችና ሕዝብ ተስማምተው፣ ተቀናጅተውና ተናብበው ለአንድ ሀገራዊ ዓላማ በጋራ መቆም በመቻላቸው የመሆኑን እውነት በልኩ ልንገነዘበው ይገባል፡፡

ኢትዮጵያውያን ልዩነቶቻቸውን በሙሉ ወደጎን በመተው ብሔራዊ ጥቅምን በማስቀደም የግል ፍላጎቶችን ከሀገር ክብር በታች በማድረግ ወደ አንድ የድል ግንባር ተምመው ለዛሬው ትውልድ ነፃ ሀገር ጥለው አልፈዋል። ጀግኖች አባቶች ይህን ሕያው ታሪክ ለማኖር ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖላቸው አልነበረም። ይልቁንም በወቅቱ በርካታ ፈተናዎች ነበሩ። ከተፈጥሮ በሽታና ድርድር፣ ከሰው ሠራሽም የውስጥ ባንዳዎች ተግዳሮት ሆነውባቸው ነበር። ሆኖም ለዓላማቸው በመጽናት ፈተናዎችን ተቋቁመው ዛሬ የሚዘከር ለትውልዱም ስንቅ የሚሆን የሚመነዘር ታሪክን ጻፉልን።

እናም ዋናው ቁም ነገር ከዓድዋ ድል አዲሱ ትውልድ ምን ይውሰድ ነው። የነበሩ ድሎችን በመዘከር ብቻ ሳይሆን አሁን ወቅቱ የሚጠይቀውን የአርበኝነት መንፈስ ተላብሶ በአባቶቻችን ደም የከበረችዋን ሀገር በላባችን ማጽናት ያስፈልጋል። በጊዜው የነበሩት ፈተናዎች አይነታቸውን ቢቀይሩም ዛሬም ፈታኞች እና ፈተናዎች አሉ፤ ይኖራሉም።

የዚህ ትውልድ መለኪያ ግን ፈተናዎችን ወደ እድል በመቀየር መሰናክሎችን በጽናት በመሻገር ለነገው ስኬት መትጋት ነው። ከጀግኖች አያት ቅድመ አያቶቻችን በወረስነው የብሔራዊ አርበኝነት መንፈስ ፀንተን በኅብረ-ብሔራዊ አንድነት ከትናንት ይልቅ ነገ ላይ አተኩረን ልንሠራ ይገባል።

በተከፈለልን ዋጋ መኖር ብቻ ሳይሆን አዳዲስ ድሎችን እያስመዘገብን አይቀሬ የሆነውን ኢትዮጵያን ወደ ከፍታዋ በመመለስ ጉዞ በድህነትና ኋላ ቀርነት ላይ በመዝመት የዓድዋን ድል መድገም ይገባል። በፈተና ውስጥም ሆነን በሕዝቦች መከባበርና መፈቃቀድ ላይ የፀናችና የተከበረች ኢትዮጵያን በማስቀጠል የአባቶቻችንን አደራ ለመጭው ትውልድ ማስረከብ ያስፈልጋል።

ከዓድዋ ጽናትን፣ አብሮነትን፤ ትጋትን፣ ብሔራዊነትንና አርበኝነትን ወርሰን በጋራ ቆመን የጋራ ሀገራችንን ወደ ከፍታዋ የመመለስ የአባቶቻችን አደራ እንዳለብን ለቅፅበትም ቢሆን መዘንጋት የለብንም!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዓድዋ የአንድነታችን ምስጢር ነው !

**ሶሎሞን በየነ**

ታሪኩ አካል ነስቶ፣ ነፍስ ዘርቶ ህያው ከመሆኑ አስቀድሞ ዓለም "ይደረጋል፣ ይፈጸማል፣ ይሆናል..." ብሎ ለቅጽበት እንኳን አስቦት አያውቅም። በዓለም ታሪክም ከዚያ ቀደምና በኋላም አልተፈጸመም። ለወደፊትም የሚፈፀም አይመስለኝም። ዛሬ ላይም ታሪኩ፣ ገድሉ፣ ሲታሰብና ሲወሳ የሆነው ነገር ሁሉ ለዓለም ሕዝብ "ህልም ነው" የሚመስለው። ነገር ግን በተባበረ ክንድና በነደደ የሀገር ፍቅር ፅኑ ተጋድሎ ታሪኩ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር፣ በዓድዋ ተራራ ግርጌ በ1888 ዓ.ም እውን ሆኗል።

አውሮፓውያን በፈረንጆቹ 1884 እና 1885 በጀርመን በርሊንግ ከተማ አፍሪካን እንደ ቅርጫ ሥጋ ከፋፍለው በቅኝ ግዛት ለመቀራመት የአህጉሪቷን ካርታ ዘርግተው ዕጣ ሲጣጣሉ፤ ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት እጣ የደረሳት ያልታደለችው ጣሊያን ነበረች። ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ሕልማቸው ሰምሮ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የአፍሪካ ሀገራትን በቅኝ ግዛት ሥር አውለዋል። ኢትዮጵያን ለመውረር ቀይ ባሕርን አቋርጦ የመጣው የጣሊያን ወራሪ ጦር ግን ያልጠበቀው ዱብዕዳ ገጥሞታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአራቱም ማዕዘን ቀፎው እንደተነካ ንብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ በ1888 ዓ.ም የካቲት 23 ቀን (ከ1895 እስከ 1896 እ.ኤ.አ) ዓድዋ ላይ የጣሊያንን ጦር ገጥሞ ድል አደረገ። ይህ የዓለምን ሕዝብ በግርምት አፉን በእጅ ያስያዘ፤ "ጥቁር ሕዝብ፣ ነጭ ሕዝብን የሚመክትበት ወታደራዊ ሳይንስም ሆነ ጥበብ እንዲሁም ሞራል የለውም" የሚለውን የተዛባና መሠረተቢስ አመክንዮና እሳቤ ፉርሽ ያደረገ ነበር።

የዓድዋ ድል ነጭ በጥቁር እንደሚሸነፍ በተጨባጭ በአደባባይ የታየበት፤ ጥቁር ሕዝብ ሁሉ የሚመካበትን አኩሪ ታሪክ አባቶቻችን አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍሰው በማይሻር፣ በማይደበዝዝ፣ በማይፋቅ ደማቅ በወርቅ የብዕር ቀለም ዓድዋ ላይ ጽፈው በክብር ያለፉበት ታሪክ የተሠራበት ነው።

አባቶቻችን ያኔ በዓለም ዙሪያ ጥቁር ሕዝብ ሁሉ በባርነት ጥላ ሥር በድቅድቅ ጨለማ ተውጦ በነበረበት ወቅት የጥቁር ሕዝብ የነጻነት ችቦን አቀጣጥለዋል። የሀገራቸውን ዳር ድንበር ሳያስደፍሩ ለመጪው ትውልድ ነፃ፣ የታፈረችና የተከበረች ሀገር አስረክበዋል። አባቶቻችን "የጥቁር ሕዝብ ሁሉ ኩራት የሆነውንና ከዚያ ቀደም ያልተፈጸመውንና ይፈጸማል" ተብሎ የማይታሰበውን ታሪክ ዓድዋ ላይ ሠርተው ያለፉበት ምስጢሩ በዋነኝነት አንድነታቸውና ለዓላማቸው በነበራቸው ፍጹም ፅናት ነበር።

ልክ እንደዛሬው ያኔም ልዩነቶች ነበሩ። ነገር ግን አባቶቻችን በመካከላቸው የነበሩ አለመግባባቶችና ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ በሀገራቸው ጉዳይ የሚያለያያቸው የአንዲት ፀጉር ዘለላ ያክል እንኳን ክፍተት በመካከላቸው አልነበረም። የሀገራቸውንም ዳር ድንበር ለማስከበርና ቅጥሯን ላለማስደፈር የነበራቸው የዓላማ ፅናት እንደ አለት የጠነከረ ነበር።

"አንድነት ኃይል፤ ጽናት የማሸነፍ ሚስጢር" መሆኑን ዓለም ላይ ከዓድዋ የተሻለ አስተማሪ ምሳሌ ያለ አይመስለኝም። በዘመኑ ዓለም ላይ አለ የተባለውን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ታጥቆ ቅኝ ሊገዛ የመጣውን የጣሊያንን ጦር፤ በየትኛውም የጦር ሳይንስ መመዘኛ "በጣም ኋላ ቀር በሆነ የጦር መሣሪያ ያውም በጋሻና በጦር ይሸነፋል" የሚል ግምት አልነበረም። ዛሬም ድረስ ይህ እንዴት ይሆናል? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ነገር ግን እውነታው አባቶቻችን በጋሻና በጦር አንገት ለአንገት ተናንቀው ወራሪውን የጣሊያንን ጦር አንገቱን አስደፍተው ወደ መጣበት የመለሱበት ምስጢሩ በነበራቸው አንድነትና ፅናት ነው።

ነጮች እንደሬት እየመረራቸውም ቢሆን ሳይወዱ በግድ የተቀበሉትንና የተጎነጩትን የሽንፈት ጽዋ፤ እኛ የኢትዮጵያውያን ደግሞ በዓለም አደባባይ ቀና ብለን ሁሌም እንድንሄድ ያስቻለንን የጥቁር ሕዝብ ሁሉ የድል በዓል የሆነውን "የዓድዋ በዓልን" በየዓመቱ በደማቅ ሁኔታ እናከብራለን፤ እንዘክራለን። እነሆ ዘንድሮም 128ኛው የዓድዋ ድል በዓል እያከበርን እንገኛለን።

አሁን ላይ በዓሉን የሚያወሱ ትልልቅ ባነሮችን አሠርቶ በየአደባባዩ በመለጠፍ፣ የጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ምስል ያለበት ቲሸርት አሠርቶ ለብሶ በየአደባባዩ ወጥቶ ከመጨፈር፣ ... ወዘተ ባለፈ በዓሉን ስናከብር "እውነት አባቶቻችን አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍሰው ይቺ ሀገር ዛሬ እኛ ላይ እንድትደርስ የከፈሉትን መስዋዕትነት ተረድተናል? ጠላትን ያሸነፉበት ሚስጥሩ ወይም ድል የነሱበት ጥበቡ ገብቶናል?" ብለን ራሳችን ልንጠይቅ ይገባል።

አባቶቻችን የጥቁር ሕዝብ ሁሉ ኩራት የሆነውን አኩሪ ገድል ዓድዋ ላይ የፈጸሙት "አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ" ተባብለው አንድነታቸውን በመጠበቃቸው ነው። ነገር ግን እኛ ልጆቻቸው ዛሬ ላይ ተከባብሮና ተባብሮ መኖር ተስኖን በግጭት አዙሪት ዋጋ እየከፈልን እንገኛለን። ለሺህ ዘመናት ያሉን ልዩነቶች ሳይገድቡን በአንድነት የኖርን ሕዝብ፤ ዛሬ ላይ በሰላም አብሮ መኖር ተስኖን ታውከናል። ያሉ ልዩነቶችን ቁጭ ብሎ በጠረጴዛ ዙሪያ ተነጋግሮ በሃሳብ ልዕልና መሸናነፍ ተስኖን ምድሪቱ የግጭት አውድማ ሆናለች።

በየዘመናቱ የተነሱብንን ጠላቶቻችን እንደሰም አቅልጠን፤ እንደብረት ቀጥቅጠን ያሸነፍንበት የኃይላችን ምስጢር አንድነታችንን ካላከበርን የእስራኤሉ መስፍን የሳምሶን እጣ ፈንታ እንደሚያጋጥመን እሙን ነው። የሳምሶን ታሪክ ከረዥሙ በአጭሩ እንዲህ ነው። እግዚያብሔር አምላክ ለሁሉም ሰው ጸጋን ሰጥቷል። ለሳምሶን ፈጣሪ የሰጠው ጸጋ ኃይልን ነው። የኃይሉ ምስጢር ደግሞ ያለው ጸጉሩ ላይ ነው ። ይህንን የተረዱት ጠላቶቹ ኃይሉን የሚያሳጡበት ወጥመድ አዘጋጁለት።

ጠላቶቹ ያለ ቦታው ተገኝቶ ባፈቀራት ገሊላ በኩል ጸጉሩን እንዲላጭ አደረጉት። ጉልበታሙ ሳምሶን የጠጉሩን ምስጢር እወቀ ጸጉሩን ለምላጭ አሳልፎ ሰጠ፤ በዚህም ኃይሉን አጣ ። በጠላቶቹ እጅ ወድቆ መጫወቻ ሆነ፤ ሁለት ዓይኑን አጥፍተው ተዘባበቱበት፣ ተፉበት፣ ተሳለቁበት፣ እንደ አሻንጉሊት ተጫወቱበት፣ አዋረዱት። ሳምሶን የተሰጠውን ጸጋ ተረድቶ በአግባቡ ሥራ ላይ ባለማዋሉ ክንዱ ዝሎ ለጠላቶቹ የጭካኔ ፈቃድ ተላልፎ ተሰጠ።

ልክ የእስራኤሉ መስፍን ሳምሶን ጉልበታሙ ፤ ጸጉሩን ሲላጭ ኃይሉን አጥቶ የጠላቶቹ መጫወቻ እንደሆነ ሁሉ፤ ውስጣዊና ውጫዊ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ደግሞ የኛ የኢትዮጵያውያን የኃይላችን ምስጢር የሆነውን አንድነታችን በመሸርሸር እንደ ቅርጫ ስጋ ከፋፍለው ተራ በተራ ሰልቅጠው ሊውጡን እንደ ጆፌ አሞራ ዙሪያ ዙሪያችን እየዞሩን ነው።

ከከፍታ ማማችን አውርደው በብሔርና በጎጥ ከፋፍለው ኃይላችን አሳጥተው አቅመ ቢስና ልፍስፍስ ሊያደርጉን እየታተሩ ነው። የኃይላችን ሚስጥር የሆነውን አንድነታችን ለማሳጣት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ይህ ደግሞ በገሃድ መሬት ላይ እየታየ ነው።

ስለዚህ የጥል ግድግዳውን ይቅር ለፈጣሪ ተባብሎ በመናድ፣ የተሰበረውን የፍቅር ድልድይ መልሶ በመገንባት፣ የተበደለውን በመካስ፣ በብሔርና በጎጥ ሳንከፋፈል፣ ከኢትዮጵያዊነት የከፍታ ማማችን ሳንወርድ ልክ እንደ ዓድዋው ከመቸውም ጊዜ በላይ በአንድነት ቆመን ጠላቶቻችን የምናሳፍርበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

የተሰጠነን ፀጋ ተረድተንና በአግባቡ ጠብቀን ልክ እንደ አባቶቻችን የሀገራችን ዳር ድንበር አስከብረን ሳትሸራረፍ ለመጪው ትውልድ ማስረከብ የዛሬው ትውልድ ታሪካዊ ኃላፊነት ነው። ይህን ሳናደርግ ሀገር እንደቅርጫ ስጋ ከተከፋፈለች ነገ ላይ በልጆቻችን ዘንድ የታሪክ ተወቃሽ ከመሆናችን ባለፈ አጽማችን በሰላም የምታርፍበት ምድር ወይም ሀገር እንዳማይኖረን ልንረዳው የሚገባ መራራ ሀቅ ነው።

ዜና

# “የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን ኅብረት ገንኖ ከእኔነት ይልቅ እኛነት ተጋምደው የታዩበት ዓውድ ነው”

-አቶ አገኘሁ ተሻገር
የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን ኅብረት ገንኖ ከኔነት ይልቅ እኛነት ተጋምደው የታዩበት ዓውድ ነው ሲሉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ።

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል የጥቁር ሕዝቦች ድል በሚል መሪ ሀሳብ ትላንት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ተከብሯል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር በበዓሉ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን ኅብረት ገንኖ የታየበት፣ መሪና ተመሪ የተናበቡበት፣ ከእኔነት ይልቅ እኛነት ተዳምረውና ተጋምደው የኃይል ክንድ የፈጠሩበት ዓውድ ነው።

የዓድዋ ድል ጨለማን በብርሃን የገረሰሰ፣ ሐሰትን ለእውነት ያስገበረ ነው ያሉት አፈ ጉባኤው፤ የበላይነትን ክፉ እሳቤ ሰብሮ እኩልነትንና የአይበገሬነት ጸሐይን ለመላው ዓለም ወጥታ የታየችበት ድል ነው ብለዋል።

ዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን ኅብረት ገንኖ የታየበት፣ መሪና ተመሪ የተናበቡበት፣ ከኔነት ይልቅ እኛነት ተዳምረውና ተጋምደው ኃይል ክንድ የፈጠሩበት ዓውድ መሆኑን ጠቅሰው አብሮነት፣ መናበብና አንድነት ሲደመሩ ወኔን ጉልበትንና ጥበብን ፈጥረው ድል ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ስሟ ገንኖ የታየበት፣ ኢትዮጵያዊነት የክብር መጠሪያ የሆነበት መሆኑን በመግለጽ፤ ድሉ በባርነት ሲማቅቁ ለነበሩ የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ስንቅና ትጥቅ ሆኖ ለነፃነታቸው እንዲታገሉ ማድረጉን ተናግረዋል።

የዓድዋ ድል የተነጣይነትን ስሜት የገደለ የወል እውነትንና አብሮነትን በጽኑ መሠረት ላይ ያኖረ መሆኑን የገለጹት አፈ ጉባኤው፤ ድሉ ቅኝ ገዢዎች በጥቁሮች ላይ የነበራቸውን የሐሰት ትርክት በእውነተኛው የእኩልነት ትርክት የቀየረ የዓለም የታሪክ ክስተት ነው ብለዋል።

ድሉ የአይቻልም መንፈስን በመስበር የሰው ልጅን እኩልነት በዓለም አደባባይ ያስመሰከረ መሆኑን ጠቅሰው፤ የቅኝ ገዢዎችን የበላይነት በሚታመንበት የጨለማ ዘመን አዲስ እውነትን ያዘለች ጸሐይ በሰንሰለታማው የዓድዋ ተራሮች አናት ወለል ብላ እንድትወጣ ማድረጉን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያኖች የመሪያቸውን ጥሪ ተቀብለው ዘር፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ ሳይገድባቸው ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በኅብረት መትመማቸውን አውስተው፤ የጠላትን ኃይል ዓድዋ ላይ ድባቅ በመምታት አሁን የሚኮራበትን ድል መቀዳጀታቸውን አስረድተዋል።

የዓድዋ ድል የመላው ዓለም የጥቁር ሕዝቦች ድል ሆኖ የሚታወስ መሆኑን ገልጸው፤ ድሉ የአብሮነት ሱታፌ ውጤት መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ ድል ሕዝባዊ ፍቅርን ወንድማማችነትን በመማር ዜጎች በነፃነት የሚኖርባት የበለጸገችና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በመገንባት ሂደት የበኩላቸውን ሊያበረክቱ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡

የዘንድሮው የዓድዋ ድል በዓል የራሱን የተሰነደ ታሪክ አውጥቶ የሚናገር ታሪካዊ መታሰቢያ ሙዚየም መከበሩ ልዩ እንደሚያደርገው ጠቅሰው፤ ሙዚየሙ የዛሬው ትውልድ የተገነባበትን ድርና ማግ እንዲገነዘብ፣ በታሪኮች ላይ በመመራመር የራሱን አበርክቶ እንዲወጣ የሚያስችል መሆኑን አመልክተዋል።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ በበኩላቸው፤ የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን በአንድ ልብ በመነሳት የዓለምን ታሪክና ትርክት የቀየሩበት ድል ነው ብለዋል።

እንደ ልጅ ዳንኤል ገለጻ፤ የዓድዋ ድል አፍሪካን የመቀራመትን አካሄድን ያከሸፈና ሌሎችን ለትግል ያነሳሳ የይቻላል መንፈስ የፈጠረ ነው።

የዘንድሮው የዓድዋ ድል በዓል ታሪኩን በተግባር በሚዘክር ቦታ መከበሩ ልዩ ያደርገዋል ያሉት ልጅ ዳንኤል ጆቴ፤ በዓሉ በንግግርና በስብሰባ ብቻ ሳይሆን ታሪኩን በሚዘክሩ ተሻጋሪ ሥራዎች ጭምር ሊከበር ይገባል ብለዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ኢትዮጵያውያን ከአራቱም አቅጣጫ የተመሙበት ድል የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሰው፤ መታሰቢያ ሙዚየም መገንባት ወጣቱ ትውልድ ታሪኩን በሚገባ እንዲያጠናና የአርበኝነት መንፈሱ እንዲያድግ ዕድል የሚፈጥር መሆኑንም ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል የመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች ድል መሆኑን ጠቅሰው በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም፤ የሚገኘው የፓን አፍሪካኒዝም ሐውልት የአፍሪካውያን አንድነት ተጋድሎ የሚያሳይ መሆኑንም አስረድተዋል።

ወጣቱ ታሪኩን በትምህርት ቤት፣ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ሲማር የአርበኝነት መንፈሱ እንደሚያድግ የገለጹት ልጅ ዳንኤል የተሻለች ኢትዮጵያ ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ አሳስበዋል።



## ‹‹የአምራች ዘርፉን በማስፋፋት ሀገርን መስወጥ ካልተቻለ አባቶቻችን የሰጡን ነፃነት ቀጣይነት አይኖረውም››

-አቶ መላኩ አለበል
የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በማስፋፋትና በማሳደግ ሀገርን መቀየር ካልተቻለ አባቶቻችን የሰጡን ነፃነት ቀጣይነት እንደማይኖረው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አቶ መላኩ አለበል ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ 2016 ማስጀመሪያ መርሐግብር ዓርብ ዕለት ተካሂዷል። በመርሐግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ የአምራች ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ የጥቅል ምርት ውስጥ ያለው አስተዋፅዖ ከሰባት በመቶ አያልፍም። በአባቶቻችን ታሪክ ብቻ መኖር ስለማይቻል የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ በመገንዘብ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍም ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ ታሪክ መሥራት ይኖርብናል፡፡

አሁን ያለው ትውልድ በልማት የራሱን አዲስ ታሪክ መሥራት አለበት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ትውልዱ ጠንካራ የሥራ ባሕልን በማዳበር አምራች ዘርፉን ማሳደግ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

አምራች ዘርፉ ሀገራዊ ጥቅል ምርት ላይ የሚኖረውን ድርሻ በማሳደግ ኢትዮጵያን መቀየር ካልቻልን አባቶቻችን የሰጡንን ነፃነት ዘላቂና ቀጣይነት አለው ብሎ መናገር አይቻልም ያሉት ሚኒስትሩ፤ የኢንዱስትሪ ጉዳይ የሉዓላዊነት ጉዳይ ነው። እንዲሁም የዜጎችን ኑሮ የማሻሻልና የመቀየር ጉዳይ ነው። ነፃነት በጦርነት ብቻ የሚገኝ አይደለም፤ በኢኮኖሚ ራስን መቻልና ነፃ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ሉዓላዊነቷን አስከብረናል ያልናት ሀገር በድህነት ምክንያት ማጣትና ማሳነስ የለብንም። ይህም በአሁኑ ትውልድ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ በዓለም ላይ ያሉ የኢኮኖሚና ቴክኖሎጂ ልዩነቶች ሀገራትን በእጅጉ እያለያዩ ነው። ይህን በመገንዘብ ተወዳዳሪና የራስን ፍላጎት በራስ ማሟላት ያስፈልጋል። የኢኮኖሚ ነፃነታችን የሀገራዊ አንድነትና የዲፕሎማሲ አቅም በመሆኑ ቴክኖሎጂንና የሠለጠነ የሰው ኃይል በፍጥነት ማሟላት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል፡፡

የዓድዋን ድል ስናስብና ስንዘክር በአባቶቻችን ታሪክ ብቻ መኩራት ሳይሆን የአሁኑ ትውልድ ለመጪው ትውልድ የበለጸገች ሀገር በማስተላለፍ ጭምር መሆን እንዳለበት የገለጹት አቶ መላኩ፤ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በውስጡ የኢኮኖሚ ነፃነት፣ የሀገር ሉዓላዊነትና የአንድነት ተልዕኮዎች አሉት።ንቅናቄው በኢትዮጵያ የተሠሩ ምርቶችን ለዓለም አቀፍ ገበያ ማስተዋወቅና የገበያ ትስስር በመፍጠር ተደራሽነታቸውን ማስፋት ነው። እንዲሁም የውጭ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ኢትዮጵያ መሳብን ዓላማ ያደረገ መሆኑን አብራርተዋል ፡፡

የ2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ከተከናወነ በኋላ እንደ ሀገር ብዙ ስኬቶች መመዝገባቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ አምራች ኢንዱስትሪው እንዲያድግ አሳሪ አሠራሮች እንዲሻሻሉ ተደርጓል።ከ22 ዓመታት በላይ የቆየው የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ፀድቆ ወደ ሥራ ገብቷል።እንዲሁም የኢትዮጵያን የገቢና የወጭ ንግድ ሚዛን ማስጠበቅ የሚያስችል የተኪ ምርት ስትራቴጂ ፀድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

የ2015 ዓ.ም ኤክስፖ የታለመለትን ዓላማ በእጅጉ ያሳካ ነበር ያሉት አቶ መላኩ፤ በአምስት ቀናት ውስጥ ከ53 ሺህ በላይ ጎብኝዎች ተሳትፈውበታል።ከ125 በላይ የንግድ ስምምነቶች የተፈረሙበትና ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት የተፈጸመበት ነው ብለዋል፡፡

በ2016 ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ በርካታ አምራቾች ምርቶቻቸውን የሚያሳዩበት መድረክ ይመቻቻል። ዘላቂ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር እንደሚደረግም ጠቁመዋል፡፡

# መከላከያ ሠራዊት ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የድል መታሰቢያው ለጦር መሪዎችና አርበኞች እንዲሁም የብሔር ብሔረሰቦችን ተጋድሎ ያካተተና እውቅና የሰጠ ስለመሆኑም አንስተው፤ የዓድዋ ድል በነፃነት እጦትና በጭቆና ሲማቅቁ ለነበሩት አፍሪካውያንና ለመላው የጥቁር ሕዝቦች የተስፋ ብርሃን ሆኗል ብለዋል።

በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ አፍሪካውያንና ጥቁር ሕዝቦች ለነፃነታቸው ላደረጉት ትግል ፋና ወጊ መሆኗን በማንሳት፤ ዛሬም ለአፍሪካ አንድነትና ለፓን አፍሪካኒዝም ዓላማ መሳካት የመሪነት ሚናዋን እንደምትቀጥል ተናግረዋል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊት የዓድዋን ጀግኖች ድል ውርሱ አድርጎ በኢትዮጵያ ላይ የሚመጣን ትንኮሳ ለመመከት ሁሌም ዝግጁ ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፤ ሠራዊቱ በአንድነትና በሀገር ፍቅር ስሜት እንደሚጓዝ ጠላቶች ያውቁታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሠራዊቱን ተጋድሎ እና የጠላቶችን ሴራ ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ በሕዝብ ስም የሚነግዱ ባንዳዎች እንታገልለታለን ለሚሉት ሕዝብ ያተረፉለት ነገር ቢኖር ሞት፣ ስደት፣ ረሃብና ችግርን ብቻ ነው ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ ሕዝቡ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ እንዳይሠራ፣ አርሶ እንዳይበላ እና ልጆቹን እንዳያስተምር አድርገውታል። የሀገር መከላከያ ሠራዊት እነዚህን የሕዝብ መከራዎች እንዲያበቁ ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረገ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

የሀገር የመጨረሻ ምሽግ በሆነው ሠራዊት ላይ የተቀናጀ የማፍረስ፣ የፕሮፖጋንዳና ትንኮሳ የከፈቱ ሕልመኞች በሠራዊቱ ተጋድሎ አከርካሪያቸው መመታቱን የጠቆሙት ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ፤ ሠራዊቱ በአንድነትና በሀገር ፍቅር ስሜት እንደሚጓዝ ጠላቶች ያውቁታል። የኢትዮጵያ ሕዝብም የሠራዊቱን ተጋድሎ እና የጠላቶችን ሴራ ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል።

በበዓሉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ አገኘሁ ተሻገር፣ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የመከላከያ ሠራዊት አባላትና አመራሮች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# የዓድዋ ድል በመላው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አገልግሎቱ በመግለጫ እንዳለው፤ የዓድዋ ድል በመላው ኢትዮጵያውያን ተሳትፎና ተጋድሎ የተገኘ አስተሳሳሪ ድል ነው። የብሔር፣ የቋንቋ፣ የአካባቢና የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ሳይገድባቸው አባቶቻችን ለጋራ ዓላማ በአንድነት መስዋዕትነት ከፍለው ነፃ ሀገር እንድንረከብ ያደረገን ድል ነው።

መላው ኢትዮጵያውያን በአንድነት በከፈሉት መስዋዕትነትና በደማቸው የተፃፈ የጋራ ድልና ታሪክ አውርሰውናል ያለው መግለጫው፤ ድሉን ሊያጎናፅፉን የቻሉት በታጠቁት ዘመናዊ መሣሪያ ወይም አደረጃጀት ሳይሆን ለጋራ ዓላማ በፅናትና በአንድነት በመሰለፋቸው ነው። በመሆኑም የዓድዋ ድል ትውልድ ሊማርበት የሚገባው የዓላማ አንድነትና የፅናት ውጤት ነው ሲል ገልጿል።

መግለጫው የዓድዋ ድልን ስንዘክርና ስናከብር ልንማራቸው ከሚገቡ ቁምነገሮች አንዱ ሀገራችን በማንኛውም ወቅት የሚገጥሟትን ፈተናዎች በድልና በስኬት መወጣት እንደምትችል የዓድዋ ድል ዋነኛ ተምሳሌት መሆኑን አመልክቶ፤ ፈተናዎችን በድል ለማጠናቀቅ ነጠላ ትርክቶችን ወደ ጎን በመተው እንደ ዓድዋ ጀግኖች ከሰፈር አስተሳሰቦች በመላቀቅና ሀገርን በማስቀደም አንድ ላይ መቆምን ይጠይቃል። እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎችን በድል ለማጠናቀቅና የሀገራችንን ብልፅግና እውን ለማድረግ ከዓድዋ ጀግኖች ፅናትና አንድነት መማር ያስፈልጋል ብሏል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ አንድም ጊዜ የሌላውን ፍለጋ ጥቃትና ወረራ ፈፅማ አታውቅም ያለው መግለጫው፤ በአንፃሩ ጠላቶችዋ በተለያዩ ዘመናት በተደጋጋሚ ከሩቅና ከቅርብ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ፈፅሟል። ሆኖም ግን ኢትዮጵያውያን ተሸንፈው እጅ የሰጡበት ወቅት የለም። ሁሉንም ወራሪዎች ድል አድርገው አንገት በማስደፋት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር አስጠብቋል ነው ያለው።

ከእነዚህ የወረራ ታሪክና የድል አድራጊነታችን የሁል ጊዜ ኩራታችን የሆነው ውቅያኖስን አቋርጠው ኢትዮጵያ ላይ ወረራ በመፈፀም ሉዓላዊነታችንን ለመጋፋት የተንቀሳቀሱ የቅኝ ገዢ ሕልምና ምኞት ያከሰመው የዓድዋ ድል መሆኑን መግለጫው አውስቶ፤ ኢትዮጵያውያን ነፃነታቸውን ለማስጠበቅ የተቃጣባቸውን የኢጣሊያን ወረራ በመመከት ዓለምን ጉድ ያሰኘ ታላቅ ጀብዱ በዓድዋ ተራሮች ላይ የፈጸሙት የዛሬ 128 ዓመት፣ በየካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም እንደነበር አስታውሷል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ እንዳለው፤ የዓድዋ ድል የመላ ጥቁር ሕዝቦችን ነፃነት ያበሰረ የክፍለ ዘመኑ ታላቅ ድል ነበር። ውርደትና ሽንፈትን የተከናነበው የኢጣሊያን ጦር ሞትና ምርኮኛ ሆኖ በዓድዋ ተራሮች ላይ ቀርቷል። በዚህም ሮምን ጨምሮ የዓድዋ የድል ችቦ በመላው ዓለም ላይ ተቀጣጥሏል። ጥቁሮች ነጭን ማሸነፍ እንደሚችሉ በተግባር ያስመሰከሩበት የተጋድሎ ውጤትም ሆኖ በታሪክ ተመዘገበ። በመሆኑም የዓድዋ ድል የአይበገሬነት፣ የአትንኩኝ ባይነት የጋራ ኅብረት የተንፀባረቀበት በደመቀ የደም ቀለም የተጻፈ የመላው የጥቁር ሕዝቦች የትግል ታሪክ ነው።

የዓድዋ ድል ከኢትዮጵያውያንም አልፈው ቅኝ ለተገዙ ሕዝቦችም የነፃነት ጮራ ሆነዋል። ዛሬ ላይ ዓድዋን ስናስብ የጋራ ድልና ታሪክ መሆኑን በመገንዘብ የሚገባው ክብር በመስጠት በሚመጥነው ዓለማቀፍ ከፍታ ልክ በድምቀት ልንዘክረው ይገባል ሲል መግለጫው አብራርቷል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## “ሰው በኀዘን ምክንያት ተሰብሮ መቅረት የለበትም”

### የማጽናናት አገልግሎት ሰጪዋ ወይዘሮ ቅድስት አሳልፍ

ሰላማዊት ውቤ

ኀዘን ከሚች ይልቅ ቋሚን ይገዘግዛል። ነገር ግን “ሰው በኀዘን ምክንያት ተሰብሮ መቅረት የለበትም።” ወይዘሮ ቅድስት አሳልፍ ለዚህ ሃሳብ ማሳያ ናቸው። እንዴት ቢባል ተከታታይ በሆኑ ዓመታት ሁለት ወንድሞቻቸውንና አባታቸውን በድንገተኛ በሞት ያጡና ኀዘን ቅስማቸውን ብቻ ሳይሆን ልባቸውንም ሰብሮት ነበር። ነገር ግን የተሰጣቸውን ማጽናኛ ምክር ተቀብለው ተግባራዊ በማድረግ እርሳቸውም የሌሎች ልብ ተሰብሮ እንዳይቀር በማጽናናት አገልግሎት ተግባር ተሰማሩ።

ከዚህ የማጽናናት አገልግሎት በተጨማሪም የዓለም እርቅና ሰላም ግብረ ሠናይ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በመሆንም በሰላምና ዕርቅ ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ በመሆናቸው ወይዘሮ ቅድስት አሳልፍን በእነዚሁ ሁለት ጉዳዮች ዙሪያ በማነጋገር የዛሬ የሕይወት ገጽታ እንግዳችን አድርገናቸዋል። መልካም ንባብ፡-

#### ማንነት

ወይዘሮ ቅድስት አሳልፍ ትውልድና ዕድገታቸው አዲስ አበባ ነው። በእዚሁ ከተማ ትዳር መስርተው ሦስት ልጆችን አፍርተዋል። በየደረጃው ትምህርታቸውን ያጠናቀቁትም እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ነው። ከንግድ ሥራ መለስተኛ ኮሌጅ በሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሙያ ተመርቀው በኢትዮጵያ ማዕድን ሀብት ልማት ኮርፖሬሽን ሥር ሻኪሶና አዲስ አበባ በሚገኙ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በልዩ ልዩ የሥራ ኃላፊነት ለ25 ዓመታት ያህል በመንግሥት ሠራተኝነት አገልግለዋል።

#### ከ25 ዓመታት የመንግሥት ሥራ አገልግሎት በኋላ

ወይዘሮዋ ከ25 ዓመታት የመንግሥት የሥራ አገልግሎት በኋላ ባለፉት አስራ ሦስት ዓመታት በሙሉ ጊዜ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራ ላይ ተሠማርተዋል። በዋናነት ታላቅ ወንድማቸውን ካጡበት ከ1995 ዓ.ም. ሰኔ ወር ጀምሮ ለፈጣሪያቸው ቃል በገቡት ኀዘንተኛን የማጽናናት አገልግሎት የተሠማሩ ሲሆን በዕርቅና ሰላም ሥራ ላይም ያገለግላሉ።

ሰኔ 16 ቀን 1995 ዓ.ም. ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ለሥራ ወጥቶ ሲመለስ ከዚህ ዓለም የተለየው ወንድማቸው በአዲስ ሜካኒካል ኢንተርፕራይዝ በዋና ሥራ አስኪያጅነት ደረጃ ላይ ነበር። በደንብ የተማረና ለሀገሩ ገና ብዙ ሊጠቅም የሚችል ሰው ነበር። የመኖርያ ሠፈራቸው አንድ ላይ በመሆኑ አብረው እየወጡና እየገቡ በየዕለቱ ይገናኙ ስለነበር በድንገተኛ የመኪና አደጋ መለያየታቸው ወይዘሮ ቅድስት መንፈሳቸውን በእጅጉ ሰብሮት ነበር።

“እኔ ታላቅ ወንድሜን በድንገት ማጣቴ ከፍተኛ የመንፈስ መታወክ አድርሶብኝ ነበር” ሲሉ የኀዘን ስሜታቸውን ክብደት ይገልጹታል። በቅጽበት ከወንድማቸው የተለዩበት አጋጣሚም በመላው ቤተሰብና ወዳጅ ዘመዶቻቸው የፈጠረው ኀዘንና ድንጋጤ እንዲህ በቀላሉ የሚፋቅና የሚጠፋም እንዳልነበረም ያስታውሳሉ።

“ይህ ክፉና ዘግናኝ አጋጣሚ መከሰቱም እንኳን ለእኛ ለቤተሰቦቹ ቀርቶ ለማያውቀው ሰው ጆሮም እጅግ የከበደና የቀፈፈ፣ ኀዘኑንም ለመቀበል ያዳገተና የማይረሳ ሰቀቀንን ትቶ ያለፈ በመሆኑ የሞት መጀመሪያ የሚመስል ገጽታም ነበረው” ይላሉ።

ያችን የቀን ጎዶሎ ፈተና በእምነት የሚያሸንፉበት አቅም በጸሎት እስኪያገኙ በምድር ላይ በዓይነ ሥጋ ለማያዩት ሟች ወንድማቸው በዕለቱ ደረት እየደቁ አንብተዋል። በሰለስቱ ወደ ልቦናቸው ተመልሰው “ያዘነ ቢኖር እርሱ ይጸልይ” ባለው የመጽሐፍ ቃል መሠረት ለፈጣሪአቸው ከዚህ ጽኑ ኀዘን እንዲያወጣቸው ተንበርክከው ለምነዋል። መልሳቸውንም አገኙ።

መልስ ለሰጣቸው አምላክ ቃል ገብተው ከተንበረከኩበት ጸሎት በርትተው ተነሱ። ባገኙት መልስ ተበራተውም ቤተሰባቸውን ለማበርታትና ቃላቸውን ሊፈጽሙ በቁርጠኝነት ወሰኑ። የአገልግሎት መነሻ ቀናቸው የወንድማቸው ሰለስት የአባታቸው የሁለተኛ ዓመት ዝክር ዕለት ነበርና ይህን ቀን ሲያስታውሱ ይደነቃሉ።

በሰልስት ከመጽሐፍ ቅዱስ ያነበቡት የማጽናኛ ቃል የወይዘሮ ቅድስት የአገልግሎት መነሻ ሆነ። ወንድማቸውን ለማሰብ በቤተ ክርስቲያን ከሚደረገው ጸሎትና ጸበል ጸዲቅ ጋር ለኀዘነተኞችም የወንጌል ትምሕርትና የማጽናኛ ዝማሬ ምግበ ነፍስ ሆኖ እንዲቀርብ ማስደረጋቸው በአገልግሎቱ እንዳጠነከራቸውም ይገልጻሉ። በዚህ የምግበ ነፍስ ምክክርም ባገኙት መንፈሳዊ እውቀት በቅዱስ መጽሐፍ “ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ከመወለድ ቀንም የሞት ቀን ይሻላል። ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ ይልቅ ወደ ልቅሶ ቤት መሄድ ይሻላል።...” ያለውን እውነት በሚገባ መገንዘባቸውንም ያስረዳሉ።



ይህንን ግንዛቤአቸውንም ለብዙዎች ለማስረዳት ብዙ ሥነ ግጥሞችን አዘጋጅተዋል። ሰዎች በቁማቸው ሳሉ ሕይወታቸውን ካስተካከሉ ሞት ሟችንም ሆነ ቋሚን እንደማይጎዳ፤ ይልቁንም ከሞተው ሰው በመማር ብዙዎች ወደ ተሻለ ሰብዕና እንዲመለሱ ለማበረታታት ከኀዘን ያወጣቸውን አምላካቸውን በማመስገን በተከታዮቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ብዙ አጽናኝ መልእክቶችን ለኅብረተሰቡ ማድረሳቸውን ይገልጻሉ።

“-አቤቱ ለልቤ እንደ መከራዋ ብዛት ማጽናናትህ ነፍሴን ደስ አሰኛት፤

- የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን፤

- እኛ ራሳችን በተጽናናንበት መጽናናት ሌሎችን ደግሞ ማጽናናት እንችላለን፤

- እኔም እስከ ዛሬ በሕይወት ካሉት ይልቅ በቀድሞ ዘመን የሞቱትን አመሰገንሁ፤

-እናት ልጇን እንደምታጽናና እንዲሁ አጽናናችኋለሁ።”

በሚሉ እና በሌሎች በርካታ መነሻ ጥቅሶች የተዘጋጁትን እነኚህን የማጽናኛ ጽሑፎች ከምቹ ቤት መልቲ ሚዲያ ጋር በመሆን በሬዲዮ ሞገድ አማካኝነት ለኀዘንተኞች ባሉበት የማድረስ ዕቅድ እንዳላቸውም ነግረውናል። ዕቅዱ ከተሳካ ማንም ሰው ሬዲዮኑን ከፍቶ እያዳመጠ ሊፅናናበት ይችላል የሚል ዕምነትና ተስፋም አላቸው።

እንግዳችን ወይዘሮ ቅድስት እንደነገሩን ይሄ ዕቅድ መተግበሩ በኀዘን ወቅት ሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥን ዘግቶ የማዘን ባሕላችንን አጽናኝ መልእክቶችን በማድመጥ በጎ ልምድ ይተካልናል። የማይቀረውንም ሞት በአግባቡ በመረዳትም ከኀዘን ስብራት ድነን ከሞተው ሰው በመማር የራስን ቀሪ ዘመን በቅንነትና በትሩፋት ሥራዎች ተሰማርቶ ሕይወትን ለማቃናት ያስችላልም ባይ ናቸው።

#### መፅናናት እና ማጽናናት

ወይዘሮ ቅድስት የደረሰባቸውን ጥልቅ ኀዘን በማዳመጥ በተለይም ወላጅ እናታቸው ያሉ በመሆናቸው ለእርሳቸውና ላዘነው ቤተሰብ በየደረጃው ያለውን ክብደት እያገናዘቡ ተጽናንተው ለማጽናናት ያስቻሉአቸውን የሃይማኖት አባቶችና ወንድሞች ያመሰግናሉ። ይህ በቤተክርስቲያን አባቶችና ወንድሞች የሚሰጥ የማጽናኛ ቃል ብርታትና ጥንካሬ እንደሰጣቸው ጠቅሰው ሌሎችም እንዲሁ በኀዘን ተጎድተው ከሰውነት ተራ ወጥተው ለጉስቁልናና ለአእምሮ መረበሽ እንዳይዳረጉ አጽንተው የሚያበረታቸውን ምክር በወቅቱ ለማግኘት በራሳቸው የማይችሉ ከሆነ የቅርብ ወዳጆቻቸው እንደ እምነታቸው ይህንን ሊያደርጉላቸው ይገባል ይላሉ።

“ሰው በኀዘን ምክንያት ተሰብሮ መቅረት የለበትም” ያሚለውን አባባል የሚያረጋግጡልን ወይዘሮ ቅድስት፤ ወደ ሕሊናቸው ተመልሰውና የራሳቸውን ተሞክሮ በማካፈል እንደራሳቸው ያዘኑ ሌሎች ሰዎችን ወደ ማጽናናት ካመሩ 21 ዓመታት አስቆጥረዋል። በተደጋጋሚ “የደረሰብኝ ኀዘን ከባድ ቢሆንም ወደ ራሴ ስመለስ ከራሴ ጋር ተማከርኩ። ሌሎች ኀዘንተኞች እኔን እያዩ መበርታት አለባቸው የሚል ድምዳሜም ላይ ደረስኩ” ብለዋል።

በእርግጥ ይህን የበጎ ፈቃድ የማጽናናት አገልግሎት በጀመሩበት ሰሞን ኀዘንተኞችን ሲያገኙ የሚነግሯቸው ገጠመኝ የእርሳቸውንም ልብ እየሰበረ ይጎዳቸው እንደነበር አልሸሸጉም። እንባ እየቀደመ በእጅጉ ሲያስቸግራቸው የቆየ ቢሆንም፤ በነበራቸው ብርቱ ቁርጠኝነት እየታገዘ የማጽናናት ተግባራቸውን ዳር ለማድረስ በወንድማቸው ሰለስት የገቡት ቃል ወደ ኋላ እንዳይመለሱ አደረጋቸው።

“የደረሰብኝን እየነገርኳቸውና መውጫውንም እያሳየኋቸው ብዙዎችን ላጽናና ሞክሬአለሁ ሰዎች ተራቸው እስከሚደርስ ድረስ ማህበረሰቡን በማገልገል የተፈጠሩበትን ዓላማ ማሳካት እንዳለባቸው ማበረታታት አለብኝ ያልኩበት ሃሳብ ከብዙ ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት ፈጥሮልኛል” ይላሉ። ይህንን ኀዘንተኞችን የማጽናናት ተግባር ከግለሰብ ኀዘን ቤቶች በተጨማሪ ሃሳባቸውን ከሚደግፉ ጋር በመተባበር ሀገራዊ በሆኑ ኀዘኖችም ጭምር ተሳትፈው ውጤት እንዳዩበትም ይገልጻሉ።

ለአብነት ወደ ጎንደር ከተማ ሲጓዝ በነበረ የስካይ ባስ አደጋ የ43 ሰዎች ሕልፈተ ሕይወት የፈጠረውን ከፍተኛ ኀዘን ለማብረድ ከአገልጋዮች ጋር ያደረጉት ጥረት፣ ተድባበ ማርያም ለግንቦት ልደታ በዓል ሲጓዙ 18 ወገኖቻችን ለሕልፈት የተዳረጉበትና ሌሎች የቆሰሉበት አጋጣሚንም በማጽናናት መሳተፋቸው፣ በተለየ ሁኔታ ደግሞ የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ መጋቢት አንድ ቀን ወደ ኬንያ በመጓዝ ላይ ሳለ በገጠመው የቴክኒክ ብልሽት በኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ላይ በደረሰው አደጋ ከ35 ሀገሮች ከተውጣጡ 157 የተለያዩ ሀገር ዜጎች መካከል 17 ያህሉ ወጣት ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ከመምህራንና ከአየር መንገዱ ባልደረቦች ጋር በመተባበር የሟች ቤተሰቦችን የማጽናናት ተግባር ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ይገልጻሉ። በተደጋጋሚ በተከናወነ የማጽናናት አገልግሎት ወይዘሮ ቅድስት ተሞክሮአቸውን በመከተል በርትተው ባዩአቸው ወገኖቻቸው ደስ እንደሚሰኙም ተናግረዋል።

#### የማጽናናት ኅብረት

እንግዳችን እንደሚሉት በኀዘን ምክንያት ብዙ ሰዎች ተሰብረው ይቀራሉ። ከኀዘን በኋላ ያለ ሕይወታቸው በእጅጉ ይወሳሰባል። በከባድ ኀዘን ይመታሉ። ትውስታው ጉልበት ያሳጣቸዋል። ቅስማቸውን ሰብሮት ያልፋል። ሊያደርጉ የሚችሉትን ሁሉ እንዳይፈጽሙ ያደርጋቸዋል። ወደ አእምሮና ወደ ሌሎች ህመሞችም የሚሄዱ አንዳንድ ሰዎች አሉ። “እኔ እግዚአብሔር ረድቶኝ እንዳልፍ የሆንኩት ይሄን ምዕራፍ ነው” ሲሉም ወይዘሮ ቅድስት ወደ ኋላ መለስ ብለው ስለራሳቸው ኀዘን ያስታውሳሉ።

“እጅግ የከበደኝን ኀዘን ያቀለሉልኝ የማጽናናት ተግባር ላይ ከተሰማሩ ካሕናት አባቶች፣ መምህራነ ወንጌል ወንድሞች የሚወጡት መንፈሳዊ ቃሎች ስለሆኑ ይህንን ተሞክሮ ሌሎች እንዲያገኙት ለማድረግ የማጽናናት ህብረትን መሥረተናል” ይላሉ።

ለምሳሌ ሰዎች ባለፉ ወገኖቻቸው ስም “የእገሌ ፋውንዴሽ” እያሉ እንደሚያቋቁሙ ሁሉ የማጽናናት ህብረታቸውን “በማኅበረ ጰራቅሊጦስ (በአጽናኝ መንፈስቅዱስ)” ስም ከካሕናትና ከመምህራነ ወንጌል ጋር በመመካከር አቋቁመው ለመቀጠል እየተሰባሰቡ መሆኑን ገልጸውልናል።

እንግዳችን “ዛሬ ኀዘን ቢሆን ነገ ደስታ ይመጣል። እጅግ ብዙ ደጋጎችን በተለያየ መንገድ በሞት አጥተናል። በምድራችን ኃጢአት ሲበዛና ሰላም ሲደፈርስ ሞት ብዙዎችን ይነጥቀናል። ይህንን በመንፈሳዊ አረዳድ ተገንዝበ ደስታና ሰላምን ለማግኘት የማጽናኛ ህብረቱ አስፈላጊ ነው” ብለዋል። ይህ የማጽናኛ አገልግሎት ተሳታፊነት እርቅና ሰላም ላይ እንዲተጉም አድርጎአቸዋል።

#### የዓለም እርቅና ሰላም ግብረ ሠናይ ድርጅት

እንግዳችን ከዚህ ኀዘንተኞችን የማጽናናት ተግባር ጎን ለጎን የዓለም እርቅና ሰላም ግብረ ሠናይ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት ሥራን በበጎ ፈቃደኝነት እንዲቀበሉ አድርጓቸዋል። ድርጅቱ በ1992 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ከፍትህ ሚኒስቴር ሕጋዊ ፈቃድ በማውጣት ሀገራቸውን በወቅቱ በተለያየ ደረጃ ላይ በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆነ የሥራ መስክ እንዲሁም በንግዱ ዓለምና በሥነጥበቡ ዘርፍ ተሰማርተው በቅንነትና በታማኝነት ባገለገሉና በማገልገል ላይ ይገኙ በነበሩ ጥቂት ሰላምና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተቋቋመ ድርጅት ነው።

እንግዳችን እነዚህ ለአገራችን ምን እንሥራ ብለው ከተሰባሰቡ ቅን ኢትዮጵያውያን ጋር አባል ሆነው የፈቃድ አገልግሎቱን ከጀመሩ ወደ 13 ዓመት ሲሆናቸው በጽህፈት ቤቱ በኃላፊነት ሲያገለግሉም ሦስት ዓመት ተጠግተዋል። ድርጅቱን በመመስረትና እስከ አሁንም በዳይሬክተርነት በመምራት ላይ የሚገኙት የቀድሞው የኢትዮጵያ ክሊኒክ ባለቤት የሆኑትና በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች በዋና ሥራ አስኪጅነት ያገለገሉት የድርጅቱ መስራች ዶክተር ያዕቆብ በቀለ መሆናቸውን ገልጸውልናል።

ይህ የዓለም እርቅና ሰላም ግብረ ሠናይ ድርጅት ከሃይማኖት፤ ከፖለቲካ፤ ከጎሳና ከጾታ ወገንተኝነት ርቆ ለሰው ልጆች ሕይወት ከሚያስፈልጉ ዋና ግብአቶች ተርታ ሰላም ሊመደብ እንደሚገባው አምነው ድርጅቱን ያቋቋሙ ብዙዎች ናቸው። አሁንም እየተባባሰ የመጣው የሰላም መደፍረስ እያሳሰባቸው የሚመካከሩ ብዙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሀገርም በውጭም ሀገር ሆነው ይህ ድርጅት እንዲጠናከር ይመክራሉ። ድርጅቱንም

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## “ሰው በኀዘን ምክንያት ተሰብሮ ...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

በአማካሪነትና በበላይ ጠባቂነት ያገለግላሉ። እነኝህን ከመሰሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ለሀሐገር ሰላም መመካከርና ባለራዕዮች የመሠረቱትን ተቋም ለማስቀጠል በመጣር ላይ ናቸው።

ኢትዮጵያውያን የሌሉበት ምድር ስለሌለ ለጊዜው ድርጅቱ የሚንቀሳቀሰው በኢትዮጵያ ቢሆንም “የዓለም እርቅና ሰላም ግብረ ሠናይ ድርጅት” የሚል ስያሜን ይዟልና ነገ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ቦታ ሁሉ የሰላምና የዕርቅ ቤተሰብ እንዲኖር ለማድረግ ጥረት መኖሩንም ገልጸውልናል።

ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በሕጋዊ ተቋማትና በማኅበረሰቡ ውስጥ የተነሱ በርካታ አለመግባባቶችን በማቀራረብ አወያይቶ መፍትሔ ሰጥቷል። በተለይም በ1997 በሀገራችን ከነበረው ምርጫ ጋር ተያይዞ በመንግሥትና በመንግሥት ተፎካካሪዎች መካከል የነበረውን ቅራኔ ለመፍታት ጥረት ካደረጉት አንጋፋ የሀገር ሽማግሌዎች የሚገኙበት ተቋም መካከል ይህ ተቋም አንዱ መሆኑንም ገልጸዋል።

በኮቪድ ምክንያት አገልግሎቱ ተቀዛቅዞ ቢቆይም እንግዳችን እንደሚሉት የድርጅቱ አገልግሎት መቋረጥ የማይገባው መሆኑን በማመን እንቅስቃሴውን መቀጠሉን ያወሳሉ። “ምቹ ቤት መልቲ ሚዲያ” ከተሰኘ ተቋም ጋር ልዩ የእናቶች የሰላም ጥሪ “ልጆቼ በጡቴ፣ ልጆቼ በሞቴ፣ ልጆቼ አፈር ስሆን” በሚል የመንግሥት ተወካዮች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አባ ገዳዎች ሀደ ስንቄዎች፣ እናቶችና አባቶች እንዲሁም ሕጻናት በተገኙበት ጦርነት ይቁም ጥያቄአቸውን በጥናት የተደገፈ ዶክመንተሪም በማቅረብ ጭምር በሰፊው አስደምጠዋል።

“በጦርነት ምክንያት አጋሮቻቸውን ልጆቻቸውንና ወንድሞቻቸውን ከማጣታቸው ባሻገር በሚደርስባቸው መደፈር እና ሌሎችም ጥቃቶች የሥነ ልቦና ጉዳት የገጠማቸውን ሴቶች ማየት በእጅጉ ልብ ይሰብራል። በዚህ ዶክመንተሪም እናቶች በተለያዩ ቋንቋዎች ባደረጉት ንግግር ጦርነት እጅግ ጎጂና ልብ ሰባሪ መሆኑን በመግለጽ በይቅርታና እርቅ ሰላም እንዲመጣ በእንባ ተማጽነዋል።”

እንግዳችን እንደገለጹልን ድርጅታቸው ከሌሎች 9 ተቋማት ጋር በመተባበር “የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ” በሚል ሐምሌ 21 ቀን 2014 ዓ.ም. ለመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ለሁሉም የሃይማኖት ተቋማት መሪዎች፣ ለምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር፣ ለአባ ገዳዎች ለሀደ ስንቄዎችና ለበርካታ የኅብረተሰብ ተወካዮች ጥሪ በማስተላለፍ ልዩ የኢትዮጵያ እናቶች የሰላም ጥሪ መርሐ ግብር በማካሄድ ጦርነት እንዲቆም ጠይቀዋል። ከዚህ መርሐ ግብር ውጤት በመነሳት ከኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት አምባሳደር ሳህለ ወርቅ ዘውዴ ጋር በመገናኘትና በመወያየት ፕሬዚዳንቷና ሌሎች ከፍተኛ ሴት ሚኒስትሮችን ጨምሮ ነሐሴ 26 ቀን 2014 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል በተገኙበት መድረክ ጦርነት በአስቸኳይ ቆሞ ሁሉም ለሰላምና እርቅ እጁን በመዘርጋት ብሔራዊ የንስሃ ጥሪ እንዲደረግ የሃይማኖት አባቶች ማሳሰባቸውን አስታውሰዋል።

በዚህ ጉባዔ የተላለፉ ድንቅ ድንቅ መልእክቶች በየሚዲያው ባይቀርቡም በተዘዋዋሪ የእናቶች እንባ ምላሽ አግኝቶ በትግራይ ክልል የሚደረገው ጦርነት ቆሞ የሰላም ሂደቱ ለመጀመር መብቃቱን እንደ መልካም ውጤት የሚያዩት መሆኑንና በአሁኑ ሰዓት ደግሞ በአማራ ክልል የሚደረገው የወንድማማቾች ጦርነት እጅግ የብዙ እናቶችን ልብ እንደሰበረ ይገልጻሉ። ሁሉም ወገኖች የሰላምን መንገድ በመሻትና ችግሮቻቸውን በውይይት በመፍታት የእናቶችን እንባ ለማስቆም እንዲቻል መንግሥት ከፍተኛውን ድርሻ እንዲወስድም በእናቶች ስም አሳስበዋል። ሀገራችን በይበልጥ ዘላቂ ሠላም እንድታገኝና ሠላማዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር ከተለያዩ የሰላም ሃሳብ አራማጆች ጋር ጥረት እንደሚያደርጉም ቃላቸውን ይሰጣሉ።

የዓለም እርቅና ሠላም ግብረ ሠናይ ድርጅት ሥራውን በትጋት ይቀጥል ዘንድ አቅማቸው የፈቀደላቸውን የቀድሞ አባሎችንም ሆነ ለሀገራቸው ሰላም የሚጨነቁትን ሁሉ በማሰባሰብ አሁን ካሉት ሃምሳ ያህል አባላት ጋር አጠናክሮ ለማስኬድ ከቀድሞዎቹ አንጋፋ አባሎች ምክርና እገዛ በማግኘት በተመሳሳይ እንቅስቃሴ ካሉ በውጭ ሀገር ከሚገኙ የኢትዮጵያ ሰላም ፈላጊ ህብረቶች ጋር ተጣምሮ ለመሥራት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ገልጸዋል።

ድርጅቱ ከወመዘክር ፣ ከባህልና ቱሪዝም፣ ከሠራተኛና



ማህበራዊ ጉዳይ፣ ከኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ እንዲሁም ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት በኢትዮጵያ “ሕዝባዊ ልማትና ሰላም፣ ሚዲያና ሰላም፣ ጥበብ ለሰላም፣ ሃይማኖትና ሰላም፣ ሀገራዊ ዕሴትና ራስን ማወቅ በወጣቶች፣ ሴቶችና ሰላም፣ የዕድሮች ሁለንተናዊ የሰላምና ዕርቅ ሚና፣ ወዘተ...” የመሳሰሉ የውይይት መድረኮችን የትብብር ሰነድ በመፈራረም ሲሠራ መቆየቱን ያወሳሉ።

በተለይ የሰላም ሃሳብን የማራመድ ተግባሩን ተወካዮቹን በየክልሎች በመላክ በአርባ ምንጭና በቤኒሻንጉል ተመሳሳይ መድረኮች እንደነበሩአቸው አውስተዋል። “አባላቱ እንደ ልብ ተዘዋውረው ለመሥራት አረጋውያን በመሆናቸውና የበጀት ችግር በመኖሩ ዘግይቶ እንጂ ድርጅቱ እንደ ነበረው እቅድ በየክልሉ ቅርንጫፎች ኖሮት ቢሠራበት ዛሬ የምናየው ችግር ሁሉ አይኖርም ነበር” ይላሉ።

‹‹በኢትዮጵያ ዘላቂ የሠላም መሠረት ለመጣል አብሮ መስራት አስፈላጊ ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ቅድስት “ሰላምን በማኅበረሰቡ ውስጥ ለማስፈን ዋናውን ድርሻ መንግሥት መውሰድ እንዳለበት ደጋግመው ያሳስባሉ። ከሌሎች ጋር በቅንጅት ወደ ታች ወደ ሕብረተሰቡ ወርዶ ለመሥራት ላለው ጽኑ ሃሳብ በዋናነት እንቅፋት የሆነባቸው የበጀት አለመኖርና የሚዲያ ሽፋን አለማግኘት መሆኑን በማውሳት ይህን ለመቅረፍ የሚወዱ ሁሉ ተባብረው ቢሠሩ ዘላቂ የሰላም መሠረት መጣል እንደማያዳግት ገልጸዋል።”

### ሴቶችና ሠላም

እንግዳችን ሴቶች በሰላም ጉዳይ መሳተፋቸው ትልቅ ጠቀሜታም አለው ይላሉ። እንዳንፀባረቁት ሃሳብ እርሳቸውን ጨምሮ ሁሉም ሴቶች ሰላምን ይሻሉ። ሴቶች በጣምም ለሠላም ይመቻሉ። በሰላም እጦት የሚደርሰው ችግርም ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ይልቅ በእጅጉ የሚጎዳው ሴቶችን ነው። ምክንያቱም ልጅን ትዳርን፣ አባትን፣ መመኪያ ወንድምን ማጣት ከፍተኛ ስብራት የሚያደርሰው ሴቶች ላይ ነው።

ስለዚህ በከፍተኛ ደረጃ በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ሴቶች የበለጠ ተነቃቅተውና ምክንያታዊ ሆነው መንቀሳቀሳቸው በአሁኑ ሰዓት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱን ሲገልፁም “በምጡም፤ በመውለዱም በማሳደጉም ከፍተኛውን ልፋት የሚያደርጉትና ለሰው ልጅ ሕልውና ትልቁን ዋጋ የከፈሉት ሴቶች ከሃምሳ ዓመት በላይ አልቅሰዋል። ከእንግዲህ በኀዘን መጎዳታቸው መቀጠሉ ግፍ ነው። ይህ ግፍ እንዲቆም ሴቶች ሊነቃቁና ሰላምን በማስፈን ሂደቱ ከፍተኛውን ድርሻ ሊይዙ ይገባል።” ይላሉ።

“እንደሚታየው የፀባችን መነሻ ፤የመካረሩም፤ የጭካኔውም ተግባር በአብዛኛው የጸብ ገመድ ጉተታውም ሲከናወን የቆየውና አሁንም እየተከናወነ ያለው በወንዶች ነው” በመጽሐፍ እንደተጠቀሰው ፈጣሪ የሚጠላቸውና የሚጸየፈው ተግባር በሰፊው በምድራችን ተከናውኗል ሲሉም ያክሉበታል።

እንደ ወይዘሮ ቅድስት አባባል ሴቶች ይህ ጉዳት እንዲቀንስ በጸሎትና በጎ ሃሳብ በማፍለቅ ትውልዳቸውንና ሀገራቸውን ሊጠብቁ ይገባል። ሴቶች ሠላምን መሻታቸውን ወደፊት መጥተው በየአደባባዩ እየወጡ እየተባበሩ ሰላም ለሀገራችን፤ ሠላም ለሕዝባችን የሚለውን ዓርማ ከፍ አድርገው በማውለብለብ አላስፈላጊ የሆኑ ፀብና ክርክሮች ከሀገራችን እንዲወገዱ ማድረግ አለባቸው።

እንደእርሳቸው አባባልም ሴቶች በአሁኑ ሰዓት ትልልቅ ደረጃ ላይ መድረሳቸውና ኃላፊነትን መውሰዳቸው ይህን መልካም ሃሳብ ለማስፈጸም እድል መመቻቸቱን ያሳያል። “ትክክለኛ ሰው በትክክለኛ ኃላፊነት ቦታ በሃይማኖትም ሆነ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ እየተቀመጠ ሀገራችን ያላትን ባሕላዊና ሃይማኖታዊ እሴት በመጠቀም ከሕዝቡ ጋር እነኚህ ተቋማት ተናበው ለመሥራት ቢወስኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀገራችን ካላት ችግር ሁሉ ነፃ ትወጣለች” ሲሉም ሃሳባቸውን ገልጸዋል።

ሴቶች የሰላም ሃሳብ ላይ በመሳተፍ ባሉበት ተቋም፣ በቤተሰባቸውና በማህበራዊ አገልግሎት ዙሪያ የነቃ ተሳትፎ ቢያደርጉ መልካም እንደሆነም ይመክራሉ። እንደ እንግዳችን ሴቶች የበርካታ በጎ እሴቶች ተምሳሌቶችም ናቸው። አብዛኛዎቹን መልካም እሴቶች ለትውልድ በማስተላለፍም አርአያነት አላቸው። ለምሳሌም በእርስ በእርስ ግንኙነቶች መካከል ያሉና ለመከባበርና ለመግባባት የሚጠቅሙ የትህትና እሴቶችን በፍቅር ማስኬድን በተመለከተ እርሳቸው ከእናታቸው፤ እናታቸው ከአያታቸው በሰዎች መካከል ሰላምን ለማስፈን ይጠቀሙባቸው የነበሩትንና ያወጉላቸውን መልካም እሴቶች ዛሬ ላይ በ60 ዓመታቸው ድልድይ ሆነው ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ በእጅጉ እንደሚመኙ ገልጸውልናል። ይህ የእሴት ቅብብልም በደንብ ከተሠራበት በቀልን አስቁሞ ተባብሮ ለመሥራት እንደሚያስችልም ገልጸዋል።

### ፋይዳ

እንግዳችን እንደሚሉት እርሳቸው ስለሰላም ተግተው የሚሠሩበት የዓለም እርቅና ሰላም ግብረ ሠናይ ድርጅት ሊያከናውናቸው ያዘጋጃቸው በርካታና ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያላቸው ጥናታዊ ሰነዶች አሉት። ከላይ እንደተገለጸው ከዚህ ቀደም ውይይት ከተደረገባቸው የሰላም መድረኮች በተጨማሪ “ሕዝባዊ የውይይት ባሕል ለሰላም›› በሚል የተዘጋጀ ቋሚ የውይይትና የምክክር መርሐ ግብር፣ እንዲሁም ‹‹ምክንያታዊ ትውልድ ሰላምን ለማጽናት፣” የሚሉና ሌሎች ሰላምን ለማጽናት ፋይዳ ያላቸው የምክረ ሃሳብ ሰነዶች ስላሉ ብዙ መሥራት እንደሚቻል ገልጸዋል።

በተጨማሪም ዜጎች እርስ በእርሳቸው ተከባብረው ተዋደውና ተባብረው በመኖር ከራሳቸው፣ ከፈጣሪያቸው፣ ከመሰሎቻቸው፤ ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ታርቀው እንዲኖሩ ማበረታታትና ተገቢውን የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ይህንን ሃሳብ በአጽንኦት ማስተማር የድርጅቱ መርህ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም ከ95 በመቶ በላይ አማኝ የሆነ ሕዝብ ላላት ሀገራችን ድንቅ የሆነ አደረጃጀት ካላቸው ተቋማት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ቢሠራ ፋይዳው እንኳን ለእኛ ለጎረቤት ሀገርም ሆነ ለዓለም የሚተርፍ ነው ብለዋል።

### መልዕክት

እንደ እንግዳችን መልዕክት ሴትም፤ ወንድም፤ ልጅም፤ አዋቂም ሁሉም ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያለው የማኅበረሰባችን ክፍል ለሠብዓዊ መብት መከበር አብሮ መቆም አለበት። ሠብዓዊነት ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። ይህ ደግሞ በዜግነት ሁሉን ወደ አንድነት ያመጣዋል። ፈጣሪ ‹‹እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትዕዛዜ ይቺ ናት›› ብሎ ለሰው ልጆች የሰጠው ትእዛዝ ለሁላችን ነውና መዋደድ አለብን። የቀደመው አንጋፋ ሰላም ወዳድ ማኅበረሰብን ያፈራ የግብረ ገብ ትምህርት አሁንም ለትውልዱ መሰጠት አለበት።

ሀገርን በቡድን ሳይሆን ሰብዓዊ መብቶችን በጠበቀ የዜግነት ስሜት ማሳደግ ይገባል። ጃፓን ዛሬ ላለችበት የዕድገት ደረጃ የደረሰችው በጃፓን ውስጥ ያሉትን ጎሳዎች በአንድነት ይዛ ነው። ቻይናም ብዙ ጎሳዎች አሏት። ብዙ የበለጸጉ ሀገሮች በእኛም ሀገር ሆነ በአፍሪካ የሚታየው አይነት ችግር አይታይባቸውም። እኛ የዓድዋን ድል ስንዘክር ለብዙ አፍሪካውያን ነጻነት ተምሳሌትና ፈር ቀዳጅ ሆነን መታየታችንን ለአፍታም መዘንጋት የለብንም። ይህንን ድል የተጎናጸፍነውም አንድ በመሆናችን ነው።

ድህነት በሀገራችን ሲበረታ ተባብረን ልናሸንፈው ሲገባን ክፍተት መፍጠራችንና መለያየታችን ለወራሪ ጠላት በተዘዋዋሪ በፈቃድ እጅ ሰጥቶ መሸነፍን የሚያሳይ ነውና ሁላችን ባለን ጸጋ ይህን ችግር ለመፍታት ቆም ብለን ማሰብ ይገባናል። በውይይት የሚፈታ ችግር ሆኖ ሳለ በብዙዎች ቸልተኝነትና ራስ ወዳድነት የሀገር ሀብት ሲወድም ወገን ሲጎዳ ዳር ቆሞ ማየት ነገ ራስን የሚጎዳ በታሪክም ተወቃሽ የሚያደርግ ነውና ልናስብበትና ድርሻችንን ልንወጣ ይገባል።

ኢትዮጵያውያን የቋንቋ፤ የሃይማኖትና ሌሎች የተለያዩ ልዩነቶቻችን ውበቶቻችን ናቸውና አንድ ሕዝብ ሆነን መቀጠል አለብን። አንጋፋዎቹ የዓለም እርቅና ሠላም ግብረ ሠናይ ድርጅት መስራቾችና አባሎቻችን ከተለያየ የሀገሪቱ አካባቢዎች የመጡና ለአንድ ኢትዮጵያ ያላቸውን ፍቅር ያሳዩ መሆናቸውን መመልከት በቂ ይሆናል። ይሄን የአንድነት ተሞክሮም ለሀገር ተረካቢው ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን” በማለት መልእክታቸውን ጠቅልለዋል። እኛም ከእንግዳችን ጋር የነበረንን ቆይታ በዚህ አጠናቀናል። በሌላ ንባብ እስከምንገናኝ በቸር ቆዩን።

# የቱሪስት አስጎብኚው - ተስፋ ሰጪ ጅምሮችና የሙያ ፈተናዎች

**ዳግም ከበደ**

የቱሪስት አስጎብኚዎች ታሪካዊ ቦታዎቻችን፣ መዳረሻዎቻችን እና የቱሪዝም መስህቦች በማስጎብኘት አምባሳደሮች በመሆን ያገለግላሉ። የጎብኚዎችን ልምድ በማሳደግ እና ዘላቂ ቱሪዝምን በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። አስጎብኚነትም (Tour Guiding) ለዓለም የቱሪዝም እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከሚያበረክት ሙያ ውስጥ ይመደባል። የመስህብ ሥፍራዎችን በቱሪስቶች እይታ ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግም ቀዳሚውን ድርሻ የሚወስዱት እነዚሁ ባለሙያዎች ናቸው።

የቱሪስት አስጎብኚዎች፤ አረንጓዴ ቱሪዝምን በማስተዋወቅ፣ ቅርሶች እንዲጠበቁ፣ አዳዲስ መዳረሻዎች እንዲፈጠሩ በማበረታታት እና በመሞገት ለለውጥ የሚታገሉም ጭምር ናቸው። ስለ ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካባቢዎች ግንዛቤ ለመፍጠር የቱሪስት አስጎብኚዎች በልዩ ሁኔታ ተመራጭ ናቸው። ከቱሪስቶች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ለአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ለቱሪዝም ዘርፍ እድገት ምሰሶ ሲሆን ይታያል። የአንድ ሀገር መንግሥት የቱሪዝም ሀብቶቹን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲያገኙ ከሰራ ቅድሚያ ሊያሳድጋቸውና ሊደግፋቸው ከሚገቡ ሙያዎች ውስጥ አስጎብኚ (Tour Guide) አንዱ ሊሆን እንደሚገባ ምሁራን ሲመክሩ ይደመጣል።

ኢትዮጵያ ካለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ወዲህ ለቱሪዝም ዘርፍ ልዩ ትኩረት መስጠቷ ይታወቃል። ቱሪዝም ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ በማድረግም የፖሊሲ ማሻሻያ አድርጋለች። ያንን ተከትሎ ሰፋፊ የመዳረሻ ልማት ሥራዎች፣ የገበያና የፕሮሞሽን እቅዶች በማውጣት ዘርፉ ውጤት እንዲያመጣ እየተሠራ መሆኑን መንግሥት በተደጋጋሚ ሲገልፅ ይሰማል። በዚህ ውስጥ በዘርፉ አስጎብኚዎችን ጨምሮ የዘርፉ ባለሙያዎችን ለማፍራትም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እየሠሩ ይገኛሉ። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘርፉ የተሠማሩ ባለሙያዎች ህብረት ፈጥረው ቱሪዝም ላይ የድርሻቸውን ለማበርከት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል የቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ይገኙበታል።

ባሳለፍነው ሳምንት ዓለም አቀፍ የአስጎብኚዎች ቀን በመላው ዓለም ተከብሮ ነበር። የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎችም በመሠረቱት ማህበር አማካኝነት ይህንን ቀን ሙያዊ ጉዳዮች ላይ በመምከር፣ ሊሻሻሉ፣ ሊጎለብቱ ይገባል ያሏቸውን ሃሳቦች ከባለድርሻ አካላት ጋር ለፖሊሲ ግብዓት እንዲሆኑ በመምከር አክብረውታል።

አቶ እንደኛነው አሰፋ የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት በአህጉር ደረጃ ደግሞ የሰሜንና የምስራቅ አፍሪካ ጀነራል ማናጀር በመሆንም ይሠራል። እንደ እርሱ እምነት በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ቱሪዝምን የጀመረው እና እየመራ ያለው አስጎብኚው (Tour Guide) ነው። ከዚህ መነሻ በባለድርሻ አካላት ሙያው ላይ ያለውን አመለካከት ለማሳደግ እየሠሩ እንደሚገኙ ይገልፃል። የቱሪዝም ሚኒስቴር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አስጎብኚዎችን እየደገፈ መሆኑን አንስቶ ይህም በማያቋርጥ የሙያ ላይ አቅም ግንባታ ድጋፍ እንዲቀጥል ጥሪ ያስተላልፋል።

ማህበራቸው አስጎብኚዎች በመስክ ላይ ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ከመደበኛው ሰዓት ውጪ የማስጎብኘት አገልግሎት ይሰጣሉ የሚለው ፕሬዚዳንቱ፤ ያንን ታሳቢ ያደረገ ፍትሀዊ ክፍያ በቱር ኦፕሬተሮች ሊመደብለት እንደሚገባም ይገልፃል። በተለይ አስጎብኚው እንግዶችን ወደ መስህብ ስፍራ ይዞ በሚንቀሳቀስበት ወቅት በርካታ ችግር ሊገጥመው እንደሚችል በማንሳት ለዚህም ዓለም አቀፍን ተሞክሮ በመውሰድ የጤና ኢንሹራንስ መግባትና ዋስትናውን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ይገልፃል። የመገናኛ ብዙሃኑም በሙያው ላይ የሚስተዋሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን በመቀየር ረገድ የድርሻቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ያሳስባል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ፤ አስጎብኚዎች በቱሪዝም ዘርፍ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ባለሙያዎች መሆናቸውን ይናገራሉ። የማህበረሰብን ባህል፣ ታሪክና ተፈጥሮ ለጎብኚው በሚገባ ከማስጎብኘት ባሻገር ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ ትልቁን ድርሻ እንደሚወስዱ ይናገራሉ።

አንድ አስጎብኚ ቱሪስቱን ወደ መስህብ ሥፍራዎች በሚወስድበትና በሚያስጎበኝበት ወቅት፤ በቸልተኝነት ቱሪስቱ ፓርኩ፣ አሊያም የዱር እንስሳት የሚኖሩበት የተፈጥሮ ስፍራ ላይ የማይገቡ ተግባራት ሊፈፅም ይችላል የሚሉት አቶ ስለሺ፤ ይህንን መሰል ተግባር እንዳይፈጠር የአስጎብኚው ሚና ትልቅ እንደሆነ ይገልፃሉ። ቱሪስቶች የመጡበት ማህበረሰብ እና አመለካከት በሚጎበኙበት ማህበረሰብ ላይ ተፅእና እንዳይፈጥር፣ የአካባቢውን ባህል እንዳይበርዙ፣ ሃይማኖቱን እንዲያከብሩ ጥንቃቄ ለማድረግም ከፍተኛ ድርሻ የሚጫወት መሆኑን ይናገራሉ። የኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎችም ይህንን መርህ ተከትለው መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ያነሳሉ። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም አስጎብኚዎች ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍና ክብር እንዲያገኙ ከባለሙያዎቹና ከማህበሩ ጋር በቅርበት እንደሚሠራ ይገልፃሉ።

አቶ ቴዎድሮስ ደርበው በቱሪዝም ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ዩኒት አስተባባሪ ናቸው። ዓለም አቀፉ የአስጎብኚዎች ቀን ክብረ በዓል ላይ በተካሄደው ውይይት ላይ የአስጎብኚነትን ሙያ በተመለከተ ሙያዊ ሃሳባቸውን አጋርተው ነበር። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ለአስጎብኚነት የነበረው አመለካከት የተዛባ እንደነበር ይገልፃሉ። ቋንቋ የቻለና መንገድ የሚያውቅ ሁሉ አስጎብኚ ተደርጎ የሚቆጠርበትና የተሳሳተ እይታ የነበረበት ወቅት መኖሩንም አንስተው፤ ሙያው እንደ አንድ የትምህርት መስክ መሰጠት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተሻሻሉ ነገሮች ያሉ ቢሆንም አመለካከቱ ግን አሁንም ድረስ በሚፈለገው ልክ እንዳልተስተካከለ ይገልፃሉ።

በቱሪዝም እሴት ሰንሰለት ውስጥ አስጎብኚዎች ወሳኝ ሥፍራ ያላቸው ባለሙያዎች ናቸው የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ የኢትዮጵያ የዘርፉ ፖሊሲም ይህንን ያቀፈ መሆኑን ይናገራሉ። አስጎብኚዎች ጎብኚውን ከማህበረሰቡ፣ ከእሴቶቹ፣ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የሚያገናኝ ድልድይ በመሆኑ እጅግ ወሳኝ ሚና ያለው እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ይላሉ።

‹‹የአስጎብኚነት ወሳኝ ሚና አንዱ መገለጫ የኢትዮጵያን ገፅታን በመገንባት ረገድ የሚወስደው ድርሻ ነው›› የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ የሀገር ገፅታ በሰው የሚገለፅ እንደሆነ ይናገራሉ። በመሆኑም አንድ አስጎብኚ በመልካም ሥነምግባር፣ በበቂ እውቀትና እንግዳ ተቀባይነትን በተላበሰ የአገልጋይነት ስሜት ጎብኚዎችን ተቀብሎ፣ ደህንነታቸውን መጠበቁን አረጋግጦ የሚፈልጉትን የመስህብ ሥፍራ እንዲጎበኙ የሚያስችል መሆኑን ያነሳሉ። ይህም የኢትዮጵያን ገፅታ የሚገነባው በመልካም ስም ለቀሪው ዓለም ኢትዮጵያን ማስተዋወቅ ሲችል እንደሆነ ይገልፃሉ። ጎብኚው አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ከጋይዱ ጋር መሆኑን በመግለፅም ከዚህ አንፃር ሀገርን ለማስተዋወቅ ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ ይናገራሉ። ከዚህ አኳያ አስጎብኚዎች ኃላፊነትን የሚወስዱና በእሴት ሰንሰለቱ ላይ ወሳኙን ሚና የሚጫወቱ መሆኑን ይገልፃሉ።

አቶ ቴዎድሮስ የአስጎብኚው ሚናን የሚያጎላው ሁለተኛው ጉዳይ መረጃ መስጠት እንደሆነ ይናገራሉ። አንድ መረጃ ብቻውን ሕይወት አይኖረውም በማለትም ያንን በሚገባ ተርጉሞና ሕይወት ሰጥቶ ለጎብኚው የሚያቀርበው አስጎብኚው መሆኑን ይገልፃሉ። ይህም ሙያው ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻውና ቱሪስቱ የኢትዮጵያን ቅርሶች፣ ተፈጥሮ ቦታዎች፣ ታሪኮች ጠንቅቆ እንዲያውቅ ለማስቻል ሙያውን በሚገባ ማክበርና ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ። በዚህ ምክንያት አስጎብኚነት ካለው የሥራ ባህሪ የሚመነጭ እጅግ ወሳኝ የሆነ የቱሪዝም እሴት ሰንሰለት ቁልፍ ሚና ያለው ዘርፍ መሆኑን ይናገራሉ።

‹‹ሙያው ውስጥ ማንም ሰው ለመሥራት ስለፈለገ ብቻ የሚገባበት መሆን የለበትም›› የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ ደርበው፤ መርህ ያለው፣ ሙያዊ መመሪያና ሥነምግባር ደንብ የያዘ በመሆኑ አንድ በሙያው ላይ መሰማራት የፈለገ ግለሰብ በትምህርት፣ በልምድና በልዩ ልዩ መንገድ ባካበተው እውቀት መሆን እንዳለበተ ነው የሚገልጹት። ለዚህም ባለሙያዎቹም ሆኑ የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሙያውንና ሙያተኛውን ማስከበር እንደሚጠበቅባቸው ይገልፃሉ።

አቶ አሸናፊ ካሳ የቱሪስት አስጎብኚ ባለሙያዎች ማህበር የቀድሞ ፕሬዚዳንትና ለ18 ዓመታት በአስጎብኚነት የሰራ የዘርፉ ባለሙያ ነው። እርሱ ደግሞ በሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ክስተቶች ሙያው ላይ የሚደርሱ እክሎችን ባለሙያው ተሻግሮ ስኬታማ ለመሆን ከልምዱ ተነስቶ መደረግ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ምክረ ሃሳብ ይሰጣል።

የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ መስህቦች፣ ቅርሶች ሌሎችም የቱሪዝም እሴቶችን ቱሪስቱ በሚገባ የሚያውቀው ከአስጎብኚው መሆኑን የሚናገረው አቶ አሸናፊ ካሳ፤ ይህ ማለት አስጎብኚው ሥነ አእምሯዊ ጉዳይ የያዘና ኢትዮጵያን ለቀሪው ዓለም የማስተዋወቅ አቅም ያለው አምባሳደር መሆኑን ይናገራል። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ (ድርቅና መሰል አደጋ) እንዲሁም ሰው ሠራሽ በሆነ ጦርነትና ግጭት ገፅታን የሚያበላሹ አጋጣሚዎች በየገዜው እንደሚከሰትና የቱሪዝም እድገት ላይ ተፅእኖ እየፈጠረ እንደሚገኝ ይናገራል።

‹‹አስጎብኚው ይህንን ችግር ተቋቁሞ የኢትዮጵያ ገፅታ እንዳይበላሽ ሙያውን እንደ ምቹ አጋጣሚ ሊጠቀምበት ይገባል›› የሚለው፤ አቶ አሸናፊ፤ ባለሙያ እራሱን በትምህርት በልምድ እንዲሁም ብቁ አድርጎ በማዘጋጀት የሀገሪቱ የውስጥ አምባሳደር መሆን እንደሚጠበቅበት ይናገራል። ቅርሶችን፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን በቀዳሚነት መንከባከብና የሀብቶቹ ጠባቂ መሆን ያለበትም ባለሙያው እንደሆነ ይናገራል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ የኮቪድ ወረርሽኝና ጦርነት ባጋጠመ ወቅት ቀጥተኛ ተጎጂ የነበረው አስጎብኚው ነበር በማለትም መሰል ችግሮችን ተቋቁሞ የኢትዮጵያን የቱሪዝም እድገት ላይ የጎላ ድርሻ ለመጫወት መትጋት እንደሚያስፈልግ ያስረዳል።

### እንደ መውጫ

ልምድ ያላቸው አስጎብኚዎች ጉዞዎችን አስደሳች እና አስተማሪ ያደርጋሉ። ከዚህም በላይ የሀገራቸው አምባሳደር በመሆን የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር ምክንያት ይሆናሉ። የቱሪዝም መስህብ ቦታዎችን በተመለከተ ሰፊ እውቀት፣ የታሪክ እውነታዎች አላቸው። በሙያው ውስጥ ለብዙ ዓመታት በመቆየታቸው ምክንያት ቱሪስቶች ቆይታቸው አዝናኝ፣ አስተማሪና በትዝታ የተሞላ እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ። በጠቅላላው የእግር ጉዞ ወይም የጉዞ ጉብኝት ልምድ ባለው አስጎብኚ ሲታገዝ ስኬታማ ይሆናል። ለዚህ ነው አስጎብኚዎች በቱሪዝም እሴት ሰንሰለት ውስጥ ቁልፍ ድርሻ አላቸው የሚባለው።

በዘመናዊው ዓለም አብዛኛዎቹ ሰዎች መጎብኘት ይወዳሉ። እንስሳትን፣ እፅዋትን፣ ሸለቆዎችን፣ ወንዞችን፣ ታሪካዊ ቦታዎችን እና ሌሎች የውሃ አካላትን እንዲሁም ኮረብቶችን እና ተራሮችን የሚያካትት ተፈጥሮን ለማየት የቱሪዝም ቦታዎችን መጎብኘት ከምርጥ ተሞክሮዎች አንዱ ነው። ነገር ግን፣ ይህ ልምድ ያለ አስጎብኚዎች እገዛ የተሟላ አይሆንም። በጠቅላላው የቱሪዝም ቦታዎችን በሥርዓት በማስጎብኘት ደንበኛውን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይወስዳሉ። ከእንስሳት ጋር እንዴት እንደሚገናኙ እና የፓርኮች አጠቃላይ ገጽታ ላይ ሰፊ እውቀት እንዴት ማግኘት እንደሚቻል አስጎብኚዎች ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህንን መሠረት አድርገው የቱሪስቱን ፍላጎት ያሟላሉ።

አንድ ቱሪስት ስለሚጎበኘው ቦታ ባህላዊ ቅርስ እና የማይረሳ ጉዞ እንዴት እንደሚያሳልፉ የተሟላ መረጃ ያለው አስጎብኚው (Tour Guide) ነው። ለዚህ ነው የአንድ ሀገር የቱሪዝም ፖሊሲ አስጎብኚዎች ሙያዊ ብቃታቸውን ለማሳደግ በሚያደርጉት ጥረት ላይ ዘላቂ ድጋፍ ማድረግ የሚያስችል ማእቀፍ ሊኖረው ይገባል የሚባለው።

**አንድ ቱሪስት ስለሚጎበኘው ቦታ ባህላዊ ቅርስ እና የማይረሳ ጉዞ እንዴት እንደሚያሳልፉ የተሟላ መረጃ ያለው አስጎብኚው (Tour Guide) ነው**

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ታላቁ ታሪክ ዓድዋ

ዋለልኝ አየለ



እነሆ የየካቲት ወር ታላቁ ታሪክ፣ የኢትዮጵያም ታላቁ ታሪክ ዓድዋ ትናንት ተከበረ። ዓድዋ፣ ትናንት ዛሬም፣ ነገም ነውና እነሆ በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ታላቁን የዓድዋ ታሪክ እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን እናስታውስ።

ከ18 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 18 ቀን 1998 ዓ.ም ስመ ጥሩ ባለቅኔ ፀጋዬ ገብረመድኅን አረፈ።

ከ11 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 21 ቀን 2005 ዓ.ም አቡነ ማትያስ፤ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ሆነው ተመረጡ።

ከ12 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት 23 ቀን 2004 ዓ.ም ደራሲና ጋዜጠኛ ማሞ ውድነህ አረፈ።

ልክ ከዛሬ 40 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት በዛሬዋ ቀን የካቲት 24 ቀን 1976 ዓ.ም  በዓሉ ግርማ ከቤቱ ወጥቶ ቀረ። እስከ አሁን ድረስ የት፣ እንዴት፣ እና በምን እንደሞተ ያልታወቀው (መሞቱ ራሱ ያልተረጋገጠው) ደራሲ እና ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ ከሥራዎቹ ያላነሰ አጠፋፉም አነጋጋሪ ሆኖ ቀጥሏል።

ከዛሬ 101 ዓመታት በፊት በዛሬዋ ቀን የካቲት 24 ቀን 1915 ዓ.ም ዝነኛውና አንጋፋው «ታይም» መጽሔት መታተም ጀመረ።

ወደ ዓድዋ ታሪካችን እንመለስ። ዓድዋን ስናስታውስ ከ28 ዓመታት በፊት በ1988 ዓ.ም 100ኛ ዓመቱ ነበር። 100ኛ ዓመቱ እንዴት እንደተከበረ ከ35 ዓመት በታች የሆነ ወጣት ብዙም አያስታውስም። በወቅቱ የመገናኛ ብዙኃን ተደራሽነቱ ጠባብ ስለነበር ከከተማ ነዋሪ ውጭ ያለው ማህበረሰብ ሁነቱን አያስተውልም ማለት ይቻላል።

ዕለታዊ ሁነቶችን እየዘገበ ታሪክ የሚሰንደው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የወቅቱን ሁነቶች ሰንዶ አስቀምጦልናል። የካቲት ወር ከገባ የመጀመሪያው ሳምንት ጀምሮ ሁነቶች የነበሩ ቢሆንም በዋዜማው ሰሞን የካቲት 21 ቀን 1988 ዓ.ም በታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ስለዓድዋ በዓል አከባበር የወጣውን ፕሮግራም  ለአሁኑ አንባቢ እናስታውስ።

በዕለቱ (በ23 ማለት ነው) ከሌሊቱ 10፡00 የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ይከናወናል። ከማለዳው 12፡00 አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ደወል ያሰማሉ። በዚሁ ሰዓት መድፍ ይተኮሳል። ከማለዳው 1፡00 በዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ ሥነ ሥርዓቱ መካሄድ ይጀምራል።

በተመሳሳይ በዓድዋ ከተማ ከሌሊቱ 10፡00 የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ይካሄዳል፤ ከማለዳው 12፡00 በዓድዋ ከተማ የሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ደወል ያሰማሉ። ከማለዳው 4፡00 በዓድዋ ከተማ የአውሮፕላን ትርዒት ይካሄዳል።

እንዲህ እንዲህ እያለ የዓድዋ የድል በዓል ሞቅ ቀዝቀዝ እያለ ሲዘከር ቆይቶ በዚህ ዓመት ደግሞ 100ኛ ዓመቱን በሚያስታውስ ሁኔታ አንድ አዲስ ነገር ይዞ መጥቷል። ይሄውም የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ተገንብቶ ተመርቋል። 100ኛ ዓመቱ ሲከበር ጀምሮ የዓድዋ መታሰቢያ የመሠረት ድንጋይ እንደሚቀመጥ ሲወራ እንደቆየ በየዘመኑ የነበሩ ዘገባዎች ያሳያሉ። እነሆ ዘንድሮ እውን ሆኖ ተመርቋል። ይህ ክስተት በሚቀጥለው ትውልድ ሲታወስ ይኖራል።

ለዚህ ሁሉ መሠረት ወደሆነው የዓድዋ ታሪክ እንሂድ!

ከታዋቂው የታሪክ ጸሐፊ ጳውሎስ ኞኞ «አጤ ምኒልክ» መጽሐፍ፣ ከተክለጻድቅ መኩሪያ «አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት» መጽሐፍ፣ ከተለያዩ ድረ ገጾች እና የመገናኛ ብዙኃን ባገኘናቸው መረጃዎች የዚህ ሳምንት ክስተት የሆነውን ዓድዋ እናስታውሳለን።

የዓድዋ ታሪክ የሚጀምረው ባለፈው ሳምንት (በየካቲት 12 ሰማዕታት መታሰቢያ እንደገለጽነው) ሴራው የጀመረው ከዓድዋ ጦርነት 12 ዓመታት በፊት በፈረንጆቹ የዘመን ቀመር 1884 ነው። ይህም በታሪክ «የበርሊን ጉባዔ» እየተባለ የሚጠራው ማለት ነው። የአውሮፓ ሀገሮች በርሊን ላይ ባደረጉት ስብሰባ አፍሪካን ለመቀራመት ሲወስኑ የጣሊያን ድርሻ ኢትዮጵያ ሆነች። በነገራችን ላይ ይህ መዘዝ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በነበረው የሃያላን ሀገራት ውይይት ላይ ለተሸናፊዋ ጣሊያን ከፍተኛ አደጋ እንደጋረጠባት፣ ለኢትዮጵያ ደግሞ የዲፕሎማሲ ኩራት ሆኖ እንደነበር የአምባሳደር ዘውዴ ረታ «የኤርትራ ጉዳይ» መጽሐፍ በሰፊው ያብራራል። ዓድዋ እነ አክሊሉ ሃብተወልድ ከሃያላን ሀገራት ጋር ሲከራከሩ የታፈሩና የተከበሩ እንዲሆኑ ኩራት ሆኗል።

ኢትዮጵያ በቅድመ ዓድዋ ከወራሪዎችና ከኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር ተዋግታም ድል አድርጋለች። ከእነዚህም አንዱ በአፄ ዮሐንስ  አራተኛ ዘመነ መንግሥት  1879 ዓ.ም ዶግዓሊ ላይ በራስ አሉላ አባነጋ አዝማችነት በጣሊያን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀዳጀችው ድል ነበር። በዚህም የጣሊያን ወታደሮች ለወሬ ነጋሪ ሳይተርፉ በአሉላ አባ ነጋ ዶግዓሊ ላይ ዶግ አመድ ሆነዋል። የኢትዮጵያ ነገር በርሊን ላይ እንደታሰበው ሊሆን አልቻለም።

በጦርነቱ እንደማይሳካላት ያወቀችው ጣሊያን እንደገና ደግሞ ውል ማጭበርበር አሰበች። በመሆኑም ለዓድዋ ጦርነት ምክንያት የሆነው የውጫሌው ውል፤ በአንቀጽ 17 በጣሊያንኛ ትርጉሙ ኢትዮጵያ የጣሊያን ጥብቅ ግዛት ነች። የውጭ ግንኙነቷም በጣሊያን በኩል ይሆናል የሚለው ሐረግ መዘዝ አመጣ። በዚች መዘዘኛ አንቀጽ ምክንያት ጦርነቱ የማይቀር መሆኑ ተረጋገጠና ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ለጦርነቱ የሀገራቸውን ሕዝብ «ክተት» ጠሩ።

«አሁንም ሀገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል ። በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው፣ ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በኀዘን እርዳኝ፤ ...» የሚለውን አዋጅ ተናገሩ። እነሆ ይህ አዋጅ በብዙ ሰዎች ዘንድ በቃል ሁሉ ሳይቀር ይታወቃል።

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ አዋጁን ሲናገሩ፤ ኢትዮጵያውያን የእርስ በእርስ ግጭታቸውን፣ ውስጣዊ ችግሮቻቸውንና አለመግባባታቸውን ወደጎን ትተው፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ተጠራርተው እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደ አንድ ልብ መስካሪ  ሆነው የመሪያቸውን ጥሪ ተከትለው ወደ ጦር አውድማው ተመሙ።

በ1988 ዓ.ም የዓድዋ ድል 100ኛ ዓመት መታሰቢያ ሲከበር፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታተመ የጥናት መድበል ላይ እንደተጻፈው፤ የጦርነቱ አዝማቾች፤ ዳግማዊ አጼ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ራስ አሉላ አባነጋ፣ ራስ መኰንን፣ ራስ ሚካኤል፣ ራስ ወሌ፣ ራስ ስብሐት፣ ደጃዝማች ሐጎስ ተፈሪ፣ ራስ አባተ፣ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (ባልቻ አባ ነፍሶ) እና ዋግ ሹም ጓንጉል ናቸው።

እውቁ የታሪክ ጸሐፊው ተክለ ጻድቅ መኩሪያ እንደሚነግሩን፤ የኢትዮጵያ ተዋጊዎች የጣሊያንን ወታደር ከበው እየተፏከሩ በጥይትና በጎራዴ ሲደበድቡት የኢጣሊያ ጦር አራት ሰዓት ከተዋጋ በኋላ ሸሸት ጀመረ። በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያውያን እየተከታተሉ ሲወጉት፣ ጦር አዝማቹ ጄኔራል አልቤርቶኒ ተቀምጦበት የነበረው በቅሎ ተመቶ ወደቀ። ወዲያው ተነሥቼ አመልጣለሁ ብሎ ለመነሣት ሲጥር ከቅምጡ ሳይነሳ እየተሽቀዳደሙ የሚሮጡት ኢትዮጵያውያን ደርሰው ጄኔራሉን ማረኩት። የአንደኛው ክፍል ጦር አዛዡ ተማርኮ፣ ሠራዊቱ በጭራሽ ከጠፋ በኋላ ሁለተኛው ክፍል የጦር ሠራዊት «ራእዮ» ከሚባለው ስፍራ ላይ ሆኖ፣ ካራት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ የሦስተኛውን ክፍል የጄኔራል ኤሌናን ጦር ጨምሮ ተዋግቶ በመጨረሻ የጦር አዛዡ ጄኔራል አሪሞንዲ እዚያው ጦርነቱ ላይ ሞቶ ተገኘ።

**«አሁንም ሀገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል። በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው፣ ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ**

ከዚህም በኋላ፤ በመጨረሻ ያለው የጣሊያን ጦር በተለይ ማርያም ሸዊቶ ከሚባለው ስፍራ ላይ ተጋጥሞ ከቀድሞው የበለጠ ጦርነት ተደረገ። ይልቁንም የመጨረሻው ድል የሚፈጸምበት በመሆኑ የሁለቱም የጦር ሠራዊት ተደባልቆ በጨበጣ በሚዋጉበት ጊዜ፣ በጨበጣ በሚደረገው ዘመቻ ከኢጣሊያኖች ይልቅ ኢትዮጵያውያን በጎራዴ አነዛዘር ቀልጣፎች ነበሩ።

ይሁን እንጂ ጣሊያኖች ተስፋ በቆረጠ ኃይል እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ በጉብዝና ሲዋጉ በመጨረሻ አዛዣቸው ጄኔራል ዳቦርሚዳ በጥይት ደረቱን ተመቶ ሞተ።

የጳውሎስ ኞኞ «አጤ ምኒልክ» መጽሐፍ በወቅቱ የነበረውን ክስተት እንዲህ ይተርከዋል።

«የተተከለው ድንኳን ሲታይ ከብዛቱ የተነሳ አፍሪካ አውሮፓን ለመጠራረግ የተነሳች ይመስላል። የጦርነቱ ዕለት ኢትዮጵያውያኑ ደማቅ ቀለም ያለው ካባ ለብሰው፣ ጠመንጃና ጦር ይዘው፣ ጎራዴ ታጥቀው፣ የነብርና የአንበሳ ቆዳ ለብሰው፣ አዝማሪዎቹ እየዘፈኑ ቄሶች፣ ልጆች፣ ሴቶች ሳይቀሩ ፀሐይዋ ፈንጠቅ ስትል በተራራው ላይ በታዩ ጊዜ የጣሊያንን ጦር አሸበሩት»

በወቅቱ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የነበሩት ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም በዓድዋው የጦር ግንባር በመሰለፍ ያስተዋሉትን «አውቶ ባዮግራፊ» በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዲህ ጽፈውታል።

«የሰው ብዛት እንደ ጎርፍ ሆነ። እግረኞችም በቅሎኞችም ተደባልቀን እንርመሰመሳለን። ፈረሰኞች በጎን እያለፉን ይቀድማሉ። ይሮጣሉ! እንደተቻለን እንሽቀዳደማለን።

ጠመንጃ ሲንጣጣ ሰማን፣ መድፍ ወዲያው ያጓራ ጀመር። ተኩሱ እያደር እየባሰበት ተቃረበን፣ አረሮቹ ማፏጨት ጀመሩ። የቆሰሉ ሰዎች ተቀምጠው አገኘን። አያ ታደግ እጁን ተመትቶ ከመንገዱ ዳር ከዛፍ ሥር ተቀምጧል። ገና በሩቁ አይቶን ተጣራ፣ ቁስሉን በመቀነቱ አሰርንለት። ጥለነው እንዳንሄድ ለመነን፣ ፈይሣ ጠመንጃ የለውም፤ የቁስለኛውን ጠመንጃ ተሸከመና እዚያው ቀረ። እኔ ዝም ብዬ ወደ ግምባር አለፍኩ። የማውቀውን ሰው አንድም አላጋጠመኝም። ተኩስ ስለበዛ መሮጥ የማይቻል ሆነ። የሰውም ብዛት እንደልብ አያስኬድም።

ደጃዝማች ማናዬ እና ልጅ አስፋው  ሁለቱም ቆስለው ድንጋይ ተንተርሰው ተጋድመው አገኘኋቸው። ልጅ አስፋው (በኋላ ፊታውራሪ አስፋው) አወቀኝና ጠቀሰኝ። ዝም ብዬው እንዳላየ ሰው ወደ ግምባር ሮጥኩ። ጦራችን ተደባልቋል። ሰውና ሰው አይተዋወቅም። ሴቶች ገምቦ ውሃ እያዘሉ፣ በበቅሎዎቻቸው እንደተቀመጡ፣ ለቁስለኞች ውሃ ያቀርባሉ። ሲነጋገሩ ሰማኋቸው። «ኧረ በጣይቱ ሞት» ይላሉ። እቴጌ የላኳቸው ይሆናሉ እያልኩ አሰብኩ።

ነጋሪቱ ከግምባርም፣ ከጀርባም፣ ከቀኝም ከግራም ይጎሸማል። የተማረኩ ጣልያኖችን አየሁ። ወዲያው ምርኮኞቹ በዙ፣ አንዳንዶቹ ወታደሮች፣ ይበልጡን ጣልያኖችን እየነዱ መጡ። በኋላ የምርኮኞች ብዛት ለዓይን የሚያሰለች ሆነ፤ ድል ማድረጋችንን አወቅሁ። ጣልያኖች መዋጋታቸውን ትተው ማርኩን እያሉ ይለምናሉ። እንደዚህ የዓድዋ ጦርነት ዕለት አንድ ጥይት እንኳ ሳልተኩስ ጦርነቱ አለቀ።»

በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ የዓድዋ ጦርነት የተጠናቀቀው፤ ክብር ለጀግኖቻችን እና ታሪክን ሰንደው ላቆዩልን ጸሐፊዎች!

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# 25 ዓመታት የተሻገረው ጥምረት- ላፎንቴኖች

ቤዛ እሸቱ

“ላፎንቴኖች” ኢትዮጵያውያን አብሮ ከመብላት ባሻገር አብረው መሥራት እንደሚችሉ በተግባር ያሳዩ የሁለት ጥንድ ድምፃውያን የጋራ መጠሪያ ነው። በዛሬው የዝነኞች ገጽ ወትሮው በተለየ ሁለት ዝነኞችን የማቅረባችን ምክንያትም በትናንትናው ዕለት የካቲት 23 ቀን 2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ትልቅ ዐሻራ ካሳረፉ ከያኒያን መካከል የሚጠቀሱት የላፎንቴኖች 25ኛ ዓመት ኢዮቤልዩ በዓል በማሪዮት ሆቴል በታላቅ ኮንሰርት መከበሩን በማስመልከት ነው።

የላፎንቴኖች ትውውቅ 25 ዓመታትንም ይሻገራል። በወቅቱ “ሮያል ፓላስ በተሰኘ የምሽት ክበብ ሲሠሩ የተጠነሰሰው ወዳጅነት እስካሁን ዘልቋል። የሀገራችን አበው ነገርን ከስሩ ውሃን ከምንጩ ይላሉና በመጀመሪያ የቡድኑን አባላት የተናጠል ጉዞ ልናይ ወደድን።

ብርሃኑ ተዘራ ከአዲስ አበባ ካዛንቺስ፤ በተለይም ለገብርኤል ቤተክርስቲያን ቀረብ ካለ ቦታ የተገኘ ድምፃዊ ነው። አባት ቢሉ አያት የቤተክርስቲያን አገልጋይ ናቸው። ቤተሰቦቹ በስለት ያገኙት የስስት ልጃቸው ነውና የገብርኤል አገልጋይ እንዲሆን ተወስኖም ነበር። እሱም ይህን የቤተሰቦቹን ምኞት የሚፈጽም ልጅ ይመስል ነበር። ሰባተኛ ክፍል እስኪደርስ ድረስ ከትምህርቱ ጎን ለጎን የቤተክርስቲያን አገልጋይ ነበር።

ሰባተኛ ክፍል ሲደርስ ግን ሙዚቃ ጠልፋው ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ የታዳጊ ቡድንን ተቀላቀለ። በአቅራቢያው በሚገኘው ቀበሌ 26፤ ቀጥሎም ከፍተኛ 15 ኪነት ቡድን እያለ የሙዚቃ ሕይወቱ ቀጠለ። የደርግ መንግሥት ከሥልጣን መነሳቱና ለተወሰነ ጊዜ የኪነት እንቅስቃሴ መቋረጡን ተከትሎ እሱም ከሙዚቃ ጋር የተለያየ መስሎ ነበር። ያኔ የምሽት ክበቦች የሙዚቃ መድረኩን መቆጣጠር ጀመሩ። ብርሃኑም በ1986 ዓ.ም ሰፈሩን ሳይለቅ ካዛንቺስ በሚገኝ የራሷ ሥም የሌላት ትንሽ ቤት ሙዚቃን መሥራት ጀመረ።

ቤቱ ትንሽ በመሆኑ ምንም ሥያሜ ባይኖረውም አጠገቡ “ላፎንቴን” የተሰኘ መዋእለ ህጻናት ስለነበር እንደምልክት ያገለግል ጀመር። በሂደት የቤቱ ሥም “ላፎንቴን” በሚል በሁሉም ዘንድ ታወቀ።

ብርሃኑ በወቅቱ የተለያዩ ድምጻውያንን ዘፈን ከመዝፈኑም ባሻገር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የታዳሚን ቀልብ በሙዚቃ ወዳጆችንም ሆነ በሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ጊዜ አልፈጀበትም። ለዚህም ይመስላል በ1987 ዓ.ም ያየህይራድ አላምረው “ሮያል ፓላስ” የተሰኘ ቤት ለመክፈት ሲያስብ ካሰባቸው የቤቱ አድማቂ ድምጻውያን መካከል አንዱ እንዲሆን ያጨው።

ሌላው የሮያል ፓላስ ድምቀት እንዲሆን የታጨው ከአዲስ አበባ (መርካቶ) የተገኘው ድምጻዊ ታደለ ሮባ ነው። በመርካቶ ሠባተኛ አካባቢ የተወለደው ታደለ ከሙዚቃ እኩል ሊባል በሚችል መልኩ ለኳስ ለየት ያለ ፍቅር ነበረው። የእሱ የመኖሪያ አካባቢ በሆነው ከፍተኛ 25 ትልቅ የኪነጥበብ እንቅስቃሴ ነበር።

የኪነት እንቅስቃሴ ሊቋረጥ በተቃረበበት አካባቢ የቀበሌ 12 ታዳጊ ኪነት አባል በመሆን ቡድኑን በተወዛዋዥነት ተቀላቅሏል። በትምህርት ቤትም “ዘ ቲ በርድስ የሚሰኝ ግሩፕ መስርተው ይንቀሳቀሱ ነበር።

ታደለ በወቅቱ የእውቁን አሜሪካዊ ድምጻዊ የማይክል ጃክሰንን ከጸጉር አበጣጠር እስከ አለባበስ ለማስመሰል ስለሚጥርና የሱን ዳንሶች ይደንስ ስለነበር ቅጽል ሥሙ “ማይክል” ነበር። በዚህ መሃልም ቢሆን ኳስ ጨዋታው አልቀረም። ኳስ ተጋጥመው የእሱ ቡድን ተጋጣሚውን ሲያሸንፍ ዋና አስጨፋሪ ነበር። ካልሆነም “ማን ሞኝ አለ” ያለ ይመስላል፤ ላሸነፏቸው ተቃራኒ ቡድን በክፍያ የድል ዜማ አውራጅ ይሆናል። ይሄ የኳስ ፍቅሩ አሁንም አልተለየው። ከሀገር ውስጥ የቡና፣ ከውጭ ክለቦች የእንግሊዙ አርሰናል ደጋፊ ነው።

የድል ዜማ ሲያወርድም ሆነ በማንኛውም ጊዜ የታደለ ድምጸ መረዋነት በሰፈር ውስጥ የታወቀ ነው። የታደለን የማዜም ብቃት የሚያውቅና ድምጻዊ ኃይልዬ ታደሰን የሚያውቅ ሰው በወቅቱ ኃይልዬ ይሰራበት



ድምፃዊ ብርሃኑ ተዘራ፣



ድምጻዊ ታደሰ ሮባ፣

ወደነበረው ቦሌ (ኦሎምፒያ) ይገኝ የነበረው “ማራቶን ክለብ” ይወስደዋል። ያን ምሽት በቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በናይት ክለብ የመዝፈን እድልን አገኘ። እዛ ሲዘፍን ያየው ሰው አራት ኪሎ የሚገኘው “ፋሲካ ክለብ” እንዲዘፍን ጋበዘው። በተመሳሳይ ኒያላ ሆቴልም እንዲዘፍን ተጠራ።

ኒያላ ሆቴል በክፍያ የሠራበት የመጀመሪያ ቤት ነው። ኒያላ እየሠራ የሰፈሩ ልጆች የነበሩት ድምጻዊ አለማየሁ ሂርጶና ፒያኒስት ጸጋቸው በወቅቱ የተሻለ የነበረው አሮሰ ሆቴል ባለቤት ጎበዝ ልጅ እንዳለ በመንገር ይዘውት ሄዱ። እዛም የተሻለ እየሠራ ከቆየ በኋላ በያየህይራድ የተቋቋመውን ሮያል ፓላስ እንዲያደምቁ ከተመረጡት አንዱ በመሆኑ ቤቱን ተቀላቀለ።

ያየህይራድ አላምረው ድምጻዊ ታደለ ሮባን ይሠራበት ከነበረው አሮሰ ሆቴል፤ ድምጻዊ ብርሃኑ ተዘራን ላፎንቴን፤ ወይም “ትንሿ ቤት” በመባል ከምትታወቀው ቤት ሌሎችንም ድምጻውያን አሰባስቦ በከፈተው ሮያል ፓላስ በጋራ ሠበሰባቸው።

በወቅቱ በቤቱ ከእነሱ በተጨማሪ ድምጻዊ አበበ ተካ፣ ሂሩት (ሳንቡቃ)፣ ኪቦርዲስት ጸጋቸውና ሌሎችም ነበሩ። የታደለና የብርሃኑ ትውውቅ እንደማንኛውም ሙዚቃን በአንድ የምሽት ክበብ እንደሚሠሩ ሰዎች ነበር። በሂደት መቀራረባቸው ጠነከረ፤ ያኔ ጥብቅ ወዳጅነት መሠረቱ።

በሂደትም የራሳቸውን አድናቂ መፍጠር ቻሉ። አድናቆቱ አድናቆት ብቻ ሆኖ አልቀረም። “ለምን የራሳችሁን ቤት አትከፍቱም፤ የራሳችሁን ቤት ክፈቱ” እያሉ የሚመክሩም የሚያደፋፍሩም አድናቂዎች ተፈጠሩ። ይህንን ሃሳብ በውስጣቸው በሚያውጠነጥኑበት ወቅት ኪቦርዲስታቸው የነበረው ጸጋቸው “ሙን ላይት” የሚባል ቤት ሄዶ ሙዚቀኞቹ ሙዚቃን፤ ምግብ ቤቱ ምግብና መጠጥን እንዲያቀርቡና ገቢውን እኩል እንዲካፈሉ ሃሳብ አቀረበላቸው። በሃሳቡ እነብርሃኑምም ሆነ የሙን ላይት ባለቤቶች ተስማሙ። ታዲያ ቤቱ በነበረው ሥም ከሚቀጥል፣ ለምን ብርሃኑ በታወቀበት “ላፎንቴን” አይጠራም በሚል ሃሳብ የክለቡ ሥያሜ “ላፎንቴን” ሆነ።

ታደለና ብርሃኑ በክለቡ ቆየት ያሉ ዘፈኖችን በመዝፈን ይበልጥ ተፈላጊ ሆኑ። ያኔ ታዲያ የተለያየ አለባበስ ከመከተል ተነስተው አንድ አይነት የአለባበስ ስታይል መከተል ብሎም በሀገራችን ባልተለመደ መልኩ በጠባቂ (ጋርድ) መንቀሳቀስ ጀመሩ። ከምሽት ክለቦች በተጨማሪም የኤግዚቢሽን አድማቂም ሆነው ነበር።

በእነዚህ መድረኮች በሚያዜሟቸው ቆየት ያሉ ዘፈኖች ተወዳጅነትን አግኝተዋል። ያኔ ታዲያ በምሽት ክለቦችም ሆነ በኤግዚቢሽን ማእከል የሚጫወቷቸው ዜማዎች የቆዩ ከመሆናቸው አንጻር አይገኙምና “ለምን በካሴት አታወጧቸውም?” የሚል አስተያየት በረከተ።

በ1988 ዓ.ም ፈላጊማ ካለ በማለት ይመስላል “ተው አምላኬ” ሲሉ የሰየሙትን የመጀመሪያ አልበማቸውን ከሚጫወቷቸው ቆየት ያሉ ዜማዎች መሃል በመምረጥ አወጡ። አልበም ከማውጣታቸው አስቀድሞ በርካታ አድናቂዎችን ማፍራት ችለው ነበር። ለዚህም ይመስላል የመጀመሪያ አልበማቸውን ሲያወጡ በኤግዚቢሽን ማእከል “ተደናቂነትን ያተረፉት ላፎንቴኖች” የሚለው ሀረግ የአልበማቸው ማስታወቂያ የሆነው።

ላፎንቴኖች ሁሌ የተለየ ነገር ማድረግ መለያቸው ነው። “እንድች እንድች” የተሰኘው ሁለተኛ አልበማቸው ሲወጣ የአልበሙ ፖስተር ላይ ከታደለና ከብርሃኑ መሃል ድንክ ውሻ ነበረች። ሦስተኛ አልበማቸው ሲወጣ እውነተኛ አንበሳ ማካተት ቢሳናቸው ፖስተሩ ላይ በኤዲቲንግ አንበሳ አስገብተዋል። ላፎንቴኖች በሚለብሱት የተለየ ተመሳሳይ ልብስ እንዲሁም በሚያደርጓቸው ተለቅ ያሉ ጫማዎች፣ በሚያደርጓቸው መነጽሮች፣ በሚይዟቸው ከዘራዎች ብቻ በሁሉ ነገራቸው የተለዩና አርቲስት መሆናቸውንና ለመድረክ ያላቸውን ክብር የሚያስታውቅ ነው።

“እንድች እንድች” የተሰኘውና በ1991 ዓ.ም ያወጡት ሁለተኛ አልበማቸው ላፎንቴን የሚለውን ሥም ከብዙሃኑ ጋር ያስተዋወቀ አልበማቸው ነው። የአልበሙን መውጣት ተከትሎ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙ በርካታ ሀገራት በመዘዋወር ሥራቸውን የማቅረብ እድል ተፈጥሮላቸዋል። የአልበሙ መጠሪያ የሆነው “እንድች እንድች” እስካሁንም ተወዳጅ ሙዚቃቸው ነው።

**እንድች እንድች**
**ሰላም ውለን ካደርን**
**ሆነን ጤና**
**በቃ ከዚህ ሌላ**
**ምናለና**
**ምስጋና ይድረሰው**
**ላምላካችን**
**ፍቅር ይስጠን**
**ጤና ይስጠን**
**ለሁላችን**
**እንጫወት እንደሰት**
**ሕይወት ያልፋል እንደዘበት**
**ተጫወቱ ተደሰቱ**
**ሕይወት ያልፋል እንደዋዛ**
**በየስቱ**

“እጅ አንሰጥም” የተሰኘው ሦስተኛ አልበማቸው ላይ እጅ አንሰጥም፣ እናት ኢትዮጵያ (ባዴ ባዴሳ) የሀገሬ ሰው፣ መለየትሽ ከፋ፣ ናፈቅኋት ድሬን፣ ኧረ እንዴት፣ ልጅነቴ፣ ባባሁልሽ፣ ሠላሜ፣ አቤቱ ድንቡሼ፣ የሚሉትና ሌሎችም ሙዚቃዎች ተካተዋል።

**ከኔም ከሱጋር ሆነሽ**
**ሁሌ አንድ ላይ ሆነሽ**
**የምትኖሪው ኑሮ**
**እቱ እንደምን ደስ አለሽ**
**አንዱን ስግልሽ ይዘሽ**
**መኖሩ ይሻልሻል**
**ከዚም ከዛም ማለት ግን**
**ኋላ አንችን ይጎዳሻል ....**
**ማየት መልካም**
**ሁሉን እይው**
**ግን በትዳር**
**ቀልዱን ተይ**

ዘፈናቸው እያዋዛ ጥሩ መልእክት የሚያስተላልፍና ተወዳጅ ሥራቸው ከሆኑት ውስጥ ተጠቃሽ ነው። አራተኛ አልበማቸው የሆነው ባቡሬ (ጓደኛ) እሱም ከቀደሞዎቹ የበለጠ ተወዳጅ ሆኖላቸዋል። በአልበሙ ላይ ጓደኝነት ሲሉ፡-

ለታደለውማ

**ብርሃን ነው ጓደኛ**
**ካገናኘም አይቀር**
**አምላክ መርጦ**
**ልክ እንደኛ**
**ጓደኛ**

ሲሉ በሥማቸው ስለጓደኝነታቸው አዚመዋል። ላፎንቴኖች እድል ላላገኙ ታዳጊ ድምጻውያን እድል በመስጠት የሚያህላቸው የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። አብሮ በመሥራት ያምናሉ፤ በርካታ እድል ያላገኙ ታዳጊዎችን በብቃታቸው በመተማመን እድል በመስጠት አብረው ሠርተዋል። ለአብነትም ቴዲ አፍሮ፣ ጃኒ ራጋ፣ ዘሪቱ ከበደ፣ ሳንፎርድ፣ ትእግስት በቀለ፣ ማሚላና ኪቺኒ፣ ቶኪቻው በሙዚቃው ዓለም ከመታወቃቸው በፊት አብረዋቸው ከሠሩት መሃል ተጠቃሽ ናቸው።

ቆየት ባሉት ጊዜያት ተለያይተዋል፣ ግሩፑ ፈርሷል የሚል ወሬ በተደጋጋሚ ሲሰማ ቢቆይም፤ እነሱ ግን የ20ኛ ዓመት በዓላቸውን ብርሃኑ መኖሪያውን አድርጎ በነበረበት፤ በርካታ ባልደረቦቻቸውና አድናቂዎቻቸው በተገኙበት አሜሪካ ማክበራቸው ይታወሳል።

ጓደኝነታቸውን ሲገልጹ “ከጓደኝነት አልፈናል” ይላሉ። ከጓደኝነትም በላይ የልጆቻቸው ክርስትና አባት ሆነዋል። ብርሃኑ 25 ዓመት በጓደኝነት ለመዝለቃቸው ሚስጥሩን ሲናገር “መቻቻል” እና “በጎደለ ሞላ” ይለዋል። ለጓደኝነታቸው መዝለቅ አንዱ የጎደለውን አንደኛው እየሞላ መቆየታቸው መሆኑን ይናገራል።

ከሁለቱ ብርሃኑ ተዘራ ሠዓት በማክበር ሲታወቅ፤ ታደለ ሮባ ደግሞ የለበሷቸውን ልብስና ጫማዎች፣ ፎቶዎች፤ እንዲሁም ሽልማቶች አደራጅቶ በማስቀመጥ ይታወቃል። የወፍጮ ቤት ባለቤት ከሆነው አድናቂያቸው መድረክ ላይ እየዘፈኑ በሁለት አህያ ተጭኖ በነፍስ ወከፍ የመጣላቸው መቶ ኪሎ ጤፍ የማይረሱት ሽልማታቸው ነው። እነሱም መድረኩ ላይ ጤፉን ተደግፈው ዘፈናቸውን አቅርበዋል። ላፎንቴኖች በአብዛኛው በጋራ ቢሠሩም ሲያስፈልግ በተናጠልና ከሌሎች ጋርም በመዋሀድ ይሠራሉ። በዚህ ሂደትም ሁለቱም የግል አልበም አውጥተዋል።

በግላቸው ከሌሎች ጋር በመዋሀድ ከሠሩትና ከተወደዱ የነጠላ ዜማዎቻቸው መካከል ብርሃኑ “ያምቡሌ” ን ከቶኪቻው ጋር፣ “አምበሳው አገሳ”ን ከማዲንጎ አፈወርቅ ጋር፣ ከማሚላና ኪቺሊ ጋር “ኤሌ ኤሌ ያባ”ን በጋራ ሠርቷል። በተመሳሳይ ታደለ ሮባ አማርኛና አፋርኛ ቅልቅል የሆነውን “አጋፒዮ” የተሰኘ ዘፈን የአፋርኛ ድምጻዊ ከሆነው ሁሴን ጋር አበርክቷል። “ባቲና ብሉዝ” የተሰኘ ዘፈኑን ከፋንታ በላይ ጋር አቀንቅኗል። ታደለ ሮባ ከድምጻዊነቱም ባሻገር “የብርሃን ፈርማ” ፊልም ላይ በተዋናይነት ተሳትፏል። ከድምጻዊነቱም ባሻገር “ላላ ፕሮዳክሽን” ን በማቋቋም የተለያዩ ድምጻውያንን አልበም ፕሮዲውስ ያደርጋል፤ አልባሳትንም ለገበያ ያቀርባል።

ላፎንቴኖች በግል ቢሠሩም እርስ በእርስ መደጋገፋቸውና ተመልሰው በጋራ መሥራታቸው አይቀርም። ለዚህም በተወደደው በብርሃኑ ተዘራ ነጠላ ዜማ “ያምቡሌ” ሥያሜ የጋራ ቤት በመክፈት ሲሠሩ መቆየታቸው አንዱ ማሳያ ነው። አንዱ ለብቻው ወይም ከሌሎች ጋር በመጣመር ለሠራው ሥራ የመጀመሪያው ደጋፊ የቡድኑ አባል ነው። ላፎንቴኖች በአርቲስቶች ዘንድ ለአርቲስቶች መገናኘት ምክንያት ናቸው ይባላል። እነሱ ካሉ በርካቶች ይሰበሰባሉ፤ ሳቅ ጨዋታው ይደራል። እንዲሁም፣ በአርቲስቶች ኀዘን ወቅት ተገኝቶ ለማጽናናትም ሆነ በደስታ ጊዜ ለማድመቅ የሚቀድማቸው የለም።

ትናንት፣ የካቲት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በማሪዮት ሆቴል በርካታ አንጋፋ ድምጻውያን በተገኙበት 25ኛ ዓመት ኢዮቤልዩ በዓላቸውን በኮንሰርት አክብረዋል። በመድረኩ ከላፎንቴኖችም በተጨማሪ በርካታ አንጋፋ ድምጻውያን ሥራቸውን አቅርበዋል። ላፎንቴኖች ከሁለቱ ጥምረት ባሻገር ከሌሎች ድምጻውያን ጋርም በጋራ በማቀንቀን ይታወቃሉ። እነዚህ አብረዋቸው ያቀነቀኑ ድምጻውያን መድረኩ ላይ አብረዋቸው አዚመዋል። በቀጣይ ከኮንሰርቱ ባሻገር የላፎንቴኖችን የ25 ዓመታት ጉዞ የሚያሳይ መጽሐፍ የማሳተምና ፊልም የማሠራት እቅድ አላቸው።

# ዓለም አቀፍ

## ዩኬ ስደተኞችን ወደ ሩዋንዳ ለማዘዋወር 370 ሚሊዮን ፓውንድ ልትከፍል ነው

ዩናይትድ ኪንግደም ጥገኝነት ጠያቂዎችን ከግዛቷ ወደ ሩዋንዳ ለሚሰፍሩት ካላት እቅድ ለተወሰነው 370 ሚሊዮን ፓውንድ እንደምትከፍል የመንግሥት ወጪዎችን የሚከታተለው ተቋም ይፋ አደረገ። ዩናይትድ ኪንግደም (ዩኬ) በአምስት ዓመታት ውስጥ ወደ ምሥራቅ አፍሪካዊቷ አገር ለሚዘዋወሩ ለእያንዳንዳቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች 150 ሺህ ፓውንድ ለሩዋንዳ መንግሥት ይከፍላል።

ሌበር ፓርቲ የኦሪት ጽሕፈት ቤቱ ያወጣውን የገንዘቡን መጠን በተመለከተ "ብሔራዊ ቅሌት" ሲል የተቃወመው ሲሆን፣ የአገር ውስጥ ሚኒስቴር ግን "አንድ ነገር ለመሥራት ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል" ብሏል። የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ "አሁን አንድ እርምጃ ካልወሰድን በ2026 ለጥገኝነት ጠያቂዎች መኖሪያ የሚወጣው ገንዘብ በየዓመቱ 11 ቢሊዮን ፓውንድ ይደርሳል" ሲሉ የውሳኔውን መነሻ አብራርተዋል።

የኦዲት ሪፖርቱ ይፋ የተደረገው የዩኬ ምክር ቤት አባላት ስደተኞችን ወደ ሌላ አገር የማዘዋወሩ ዕቅድን በተመለከተ ከፍተኛ ግልጽነት እንዲኖር መጠየቃቸውን ተከትሎ ነው። ለአምስት ዓመታት በተደረሰው ስምምነት መሠረት፣ ዩናይትድ ኪንግደም በሕገወጥ መንገድ ወደ ግዛቷ የሚገቡ ሰዎችን ወደ ሩዋንዳ በመላክ እዚያ ጥገኝነት እንዲጠይቁ ይደረጋል።



የዚህ ፖሊሲ ዓላማም በእንግሊዝ ቦይ በኩል በባሕር የሚገቡ ሰዎችን ለማስቆም ሲሆን፣ ይህ ዕቅድም ጠቅላይ ሚኒስትር ሪሺ ሱናክ ከቀዳሚ ዓላማዎቻቸው መካከል አንዱ ነው። ቢሆንም ግን ዕቅዱ የሕጋዊነት እንቅፋት ስለገጠመው በእንጥልጥል ላይ ያለ ሲሆን፣ እስካሁን አንድም ሰው ወደ ሩዋንዳ አልተዘዋወረም።

ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀው ሕግ በፓርላማ አባላት የፀደቀ ሲሆን፣ በሚቀጥለው ሳምንት ክርክር ይደረግበታል። ነገር ግን አሁን ይፋ የሆነው የገንዘብ መጠን ጉዳይ እንቅፋት ሊሆን ይችላል ተብሏል። በዚህ መርሐ ግብር አማካይነት የዩኬ የሀገር ውስጥ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ለሩዋንዳ የምጣኔ ሃብት ድጋፍ እና ወደ አገሩ ለሚገቡት ሰዎች የሚውል ገንዘብ ይሰጣል።

ከአውሮፓውያኑ 2022 ጀምሮ እስካሁን ዩኬ 220 ሚሊዮን ፓውንድ ለሩዋንዳ የሰጠች ሲሆን በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታትም በየዓመቱ 50 ሚሊዮን ፓውንድ በመስጠት አጠቃላዩ 370 ሚሊዮን ፓውንድ ይሆናል። ከ300 በላይ ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ ሩዋንዳ የሚላኩ ከሆነ፣ በአንድ ጊዜ 120 ሚሊዮን ፓውንድ እና ተጨማሪ በእያንዳንዳቸው ሰዎች 20 ሺህ ፓውንድ ትከፍላለች።

በተጨማሪም ወደ ሩዋንዳ ለሚዘዋወሩት ጥገኝነት ጠያቂዎች ለእያንዳንዳቸው የመኖሪያ፣ የምግብ እና የትምህርት ወጪ የሚሆን 150,874 ፓውንድ መድቧል። ነገር ግን ግለሰቦቹ ከሩዋንዳ ውጪ የሚሄዱ ከሆነ ገንዘቡ የሚቆም ሲሆን ለጉዟቸው የሚሆን 10 ሺህ ፓውንድ ብቻ ይሰጣቸዋል።

የኦዲት ተቋሙ ባወጣው መረጃ መሠረት ይህ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ወደ ሩዋንዳ ለማዘዋወር የወጣው ዕቅድ በ370 ሚሊዮን ፓውንድ ላይ የሚቆም ሳይሆን ተጨማሪ ወጪዎች እንደሚኖሩት አሳውቋል። ተቃዋሚው ሌበር ፓርቲ በሚቀጥለው ምርጫ የሚያሸንፍ ከሆነ ወደ ሩዋንዳ ስደተኞችን ለማዘዋወር የተያዘውን እቅድ እንደሚሰርዘው አስታውቋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## አውሮፕላኑ "በሰከሩ መንገደኞች" ምክንያት የበረራ አቅጣጫውን ቀየረ




ከዩናይትድ ኪንግደም ለንደን ተነስቶ ወደ አሜሪካዋ ኒውጀርሲ እየበረረ የነበረው የአሜሪካው ዩናይትድ አየር መንገድ 'በሰከሩ ሁለት መንገደኞች' ምክንያት አቅጣጫውን ቀይሮ በሌላ ግዛት አረፈ። አውሮፕላኑ ሁለት የሰከሩ የሚመስሉ መንገደኞች "ረብሻ በማስነሳታቸው" አቅጣጫውን ቀይሮ ሜይን በተባለችው ግዛት ማረፉንም አየር መንገዱ ገልጿል።

ዓርብ ጥዋት ከለንደኑ ሂትሮው አየር ማረፊያ የተነሳው የበረራ ቁጥር ዩኤ883 አውሮፕላን ኒዋርክ ማረፍ ቢኖርበትም፣ አቅጣጫውን ቀይሮ በባንጎር ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንዲያርፍ ተደርጓል። አውሮፕላኑ ካረፈ በኋላም ፖሊስ ሁለቱን ተሳፋሪዎች ከአውሮፕላኑ እንዲወርዱ እንዳደረጋቸውም ዩናይትድ አየር መንገድ ለቢቢሲ በላከው ኢሜይል ገልጿል።

እነዚህ መንገደኞች ለወደፊቱም ከየትኛውም የዩናይትድ አየር መንገድ በረራዎች ይታገዳሉ ተብሏል። አውሮፕላኑ በአትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ ለሰባት ሰዓታት ጉዞ ካደረገ በኋላ የበረራ እንቅስቃሴዎችን የሚቆጣጠረው ፍላይትራዳር እንዳሳየው ወደ መዳረሻው ከመሄዱ በፊ አቅጣጫውን ቀይሮ ባንጎር አየር ማረፊያ ላይ አርፏል።

"ዩናይትድ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር 883 ሁለት የሰከሩ የሚመስሉ መንገደኞች ረብሻ በማስነሳታቸው በባንጎር አውሮፕላን ማረፊያ አርፏል" በማለት አየር መንገዱ በመግለጫው አትቷል። "የሕግ አስከባሪዎች ሁለቱን መንገደኞች ካስወረዷቸው በኋላ አውሮፕላኑ ወደ ቀደመ መዳረሻው ኒዋርክ ሊበርቲ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሄዷል። ጉዳዩን እስክናጣራ ድረስ ሁለቱ መንገደኞች ከማንኛውም የዩናይትድ በረራዎች ይታገዳሉ" ብሏል።

አስር የበረራ ሠራተኞችን እና 150 መንገደኞችን አሳፍሮ የነበረው አውሮፕላኑ ከለንደን ጥዋት 1፡52 ተነስቶም በሜይን አራት ስዓት ላይ በሰላም ማረፉንም የአሜሪካ የፌደራል አቪየሽን አስተዳደር መግለጹን የቢቢሲ ዘገባ አመልክቷል።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## ትውልዱ ከዓድዋ ምን ይማር?

**አስናቀ ፀጋዬ**

ስለዓድዋ ድል ብዙ ተብሏል፤ ብዙ ተነግሯል። ዓድዋ የጥቁር አርበኞች የአልበገር ባይነት ድል ነው። ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን ሉዓላዊነታቸውን ያስጠበቁበትና ቅኝ ገዢዎቻቸውን ያንበረከኩበት ትልቅ የታሪክ ዐሻራ ነው። ዓድዋ ለብዙ የአፍሪካ ሀገራት የነፃነት ተምሳሌት ነው። በርካታ አፍሪካውያን የነፃነት ትግል እንዲያደርጉ ያነሳሳ የድል ጮራ ነው። ብዛት ያላቸው የአፍሪካ ሀገራት በዓድዋ ድል ተነሳሳስተው ባደረጉት ትግል ነፃነታቸውን ከቅኝ ገዢዎች ተቀዳጅተዋል..ወዘተ።

ዓድዋ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያውያን የሚኮሩበትና በየዓመቱ የሚዘክሩት ትልቅ የድል በዓል ነው። የአፍሪካ ሀገራት ከዛም በላይ ዓለም በዓድዋ ድል አሁን ድረስ ይደነቃሉ። ቀደምት አባቶች በዓድዋ ውጊያ በዓለም ፊት ያስመዘገቡት ታሪክ ታዲያ አሁን ባለው ትውልድ በሚገባ መታወቅና መዘከር አለበት። የአሁኑ ትውል የዓድዋ ድልን በብዙ መንገድ ሊነሳሳበትና ሊጠቀምበት ይገባል ።

ይህ ትውልድ በርካታ ችግሮች አሉበት። ብዙ የሚያነሳቸው ጥያቄዎችም አሉት። ሥራ አጥነትና ድህነት በብርቱ እየፈተነው ነው። ፈተናዎች በርትተውበታል። ፈተናና የሕይወት ውጣ ውረድን ለማለፍ ታዲያ የዛሬው ትውልድ የዓድዋን የድል “የይቻላል” መንፈስ በብዙ መልኩ ሊጠቀምበትና ራሱን ሊለውጥበት ይችላል።

በወቅቱ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ባደረጉት ሀገርህን ከጠላት ወራሪ አድን ጥሪ ያ ትውልድ ፈጣን ምላሽ ሰጥቶ ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተሰባስቦ ወረኢሉ ላይ ከቷል። ይህም ለጋራ ጠላት ኢትዮጵያውያን ምን ያህል አንድነት እንዳላቸው ያሳየ ነው። ከዚህ የዛሬው ትውልድ ምን ትምህርት ሊወስድ ይገባል ?።

መላው ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ከወራሪ ለመታደግ ከንጉሡ የቀረበላቸውን ጥሪ ተቀብለው በመትመም ወረኢሉ ላይ ሲከትሙ ቀንና ለሊት በእግራቸው ተጉዘው ነው። ጉዟቸው ምን ያህል አስቸጋሪ፣ አድካሚና ፈተና እንደሆነ ዛሬ ላይ ሆኖ መገመት አያዳግትም። ይህም የያኔዎቹ አባቶች፣ እናቶችና ወጣቶች ምን ያህል የበረታ ጽኑ የአካልና የመንፈስ ጥንካሬ፣ ጀግንነትና ቆራጥነት እንደነበራቸው ያሳያል። የዛሬው ትውልድ ከዚህ ምን ሊማር ይችላል ? ።


አያት ቅድመ አያቶችና በአርበኝነት ከአራቱም የኢትዮጵያ አቅጣጫዎች ተነስተው ዓድዋ ሲዘምቱ ጉዟቸው በእግር፤ ስንቃቸው በግል ነበር። የያዙት ስንቅ ቆሎ፣ ዳቦና የቻለው ቋንጣ ነበር። የሚጠጡትም ከሀገራቸው ምንጮች የሚያፈልቁትን ውሃ ነበር። መጠለያቸው የእናት ሀገራቸው ጋራና ሸንተረር ፣ደንና ዋሻ ነበር። አርበኞች የታጠቁት መሣሪያ ከወራሪው ጣሊያን ጋር ሲመዛዘን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። እጅግ ኋላ ቀር ነበር ከዚህ ለመማር ትውልዱ ምን ያህል ዝግጁ ነው?።

በጊዜው ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን ሉዓላዊነት ላለማስደፈር በልባቸው የሰነቁት ጥልቅ የሆነ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ ፍጹም የሞራል የበላይነት፣ ልበ ሙሉነትና የማይንበረከክ ታላቅ የጀግንነት መንፈስ ነበር። ይህ የሞራል አንድነትም ነው ለድል ያበቃቸው። ይህ የዓላማ ቆራጥነት ነው በነጭ ወራሪ ላይ ድል እንዲቀናጁ ያደረጋቸው። በተመሳሳይ የዛሬውም ትውልድ ከዚህ አንጻር የት ነው ያለው ?።

ቢሆን እንዲህ አይነቱን ጥልቅ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ የተጋድሎ ሞራል፣ ልበ ሙሉነትንና የጀግንነት መንፈስን ሊላበስ ይገባል።

እንዲህ አይነቱ ስብእና የግድ ጦርነት ሲመጣ ብቻ የሚበቅል ሳይሆን በልዩ ልዩ መልኩ ሀገርን ለማሳደግና ከጠላትም ለመጠበቅ በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ሁሉ በመሳተፍ ሀገራዊ አስተዋፅኦ በማድረግ ሊደገም የሚችል ነው። በሞራልና በወኔ ራስንም ጭምር ማሳደግና መለወጥ ይቻላል። ልበ ሙሉነትና ወኔ ካለ እንዲሁም ለራስ የሚሰጥ ግምት ከፍተኛ ከሆነ ራስን በልዩ ልዩ መልኩ መለወጥ አያዳግትም። ራስን መለወጥ ከተቻለ ደግሞ አካባቢን፣ ማህረሰብንና ሀገርን መቀየር ይቻላል።

የዓድዋ ጀግኖች ሞትን ንቀው ደረታቸውንና ግንባራቸውን ለመትረየስና ለጠመንጃ ጥይት ሰጥተዋል። አንዱ ሲወድቅ ሌላው ጀግና ፎክሮ እየተንደረደረ ጠላቱን በጎራዴ እየቀነጠሰ ጦሩን ወርውሮ በጠላቱ ደረት ላይ እየሰካ ጥቁሩ አንበሣ የነጮችን እብሪት በጣጥሶ በመጣል እየሞተም፣ እየገደለም፣ እየወደቀም፣ እየተነሳም ድል አድርጓል። ይህ ትውልድ ደግሞ ዛሬ ላይ ከጀግኖች አባቶቹና እናቶቹ ቆራጥነትንና የዓላማ ፅናትን መማር አለበት። ለሀገር የሚከፈል መስዋትነት ምን ያህል እንደሚያስከብር ሊረዳ ይገባል። ለሀገሩ ብቻ ሳይሆን ለራሱም ሲል መስዋእት መክፈል ይጠበቅበታል። ያኔ እርሱም ሀገሩም ትከበራለች።



ኢትዮጵያ በታላቅ ተጋድሎ ካበሰረችው የዓድዋ ጦርነት ድል በኋላ ጥቁሮች በዓለም ላይ አንገታቸውን ቀና አድርገዋል። ከዚያን ጊዜ በኋላ በጥቁሮች የበላይነት የሚመሩ የነፃነት ንቅናቄዎች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ተፈጥረዋል። የፓን አፍሪካ ንቅናቄም የዓድዋ ድል ውጤት ተደርጎ ይቆጠራል። በጊዜው በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ አብዛኞዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ይበልጥ ተደራጅተው ለነፃነታቸው መፋለም የጀመሩት ለዓለም ተምሣሌነቱ ከተረፈው የዓድዋ ጦርነት ድል በኋላ ነው።

ኢትዮጵያውያን በአንድነት፣ በፍቅር፣ በህብረትና በታላቅ ሀገራዊ ስሜት ተሰልፈው ታላቅ ታሪካዊ ጀግንነት የፈፀሙበት ድል ነው። ጠላታቸውን ሰባብረው ጥለው ያንበረከኩበት በዓለም ፊት ማንነታቸውን ብዙ ዋጋ ከፍለው በአንጸባራቂ ድል ያስመሰከሩበት ድንቅ የታሪክ ክስተት ነው።

በወቅቱ ኢትዮጵያውያን የፈፀሙት ታላቅ ጀብድ የዛሬው ትውልድ በነፃነት አንገቱን ቀና አድርጎ እንዴሄድ አስችሎታል። አብዛኞዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ከረጅም ጊዜ ቅኝ ግዛት በኋላ ነፃነታቸውን ቢቀዳጁም ቅኝ ግዛቱ ጥሎባቸው የሄደው ጠባሳ ዛሬም ድረስ አለቀቀም። ኢትዮጵያ ግን ወራሪዋን ድል ነስታ ነፃነቷን በማስጠበቋ የዛሬው ትውልድ በኩራት ደረቱን ነፍቶ እንዲሄድ አድርጎታል።

የዛሬውም ሆነ የወደፊቱ ትውልድ ከዓድዋ ድል ብዙ ይማራል ተብሎ ይታሰባል። ዓድዋ በአንድነት የተገኘ ድል ነው። አንድነት ኃይል ነው የሚለውን እምነት ያፀና በአንድነት ውስጥ አይበገሬነት እንዳለና እንደሚኖር ያሳየ ታላቅ ተምሣሌት ነው። ተተኪው ትውልድ ይህንን የአያት ቅድመ አያቶቹን ምሣሌና አርአያነት ጠብቆ ከዓድዋም ታላቅ ትምህርት ወስዶ ሀገሩን በፍቅር፣ በህብረት፣ በአንድነት መጠበቅና ማሳደግ ይገባዋል።

የዓድዋ ታሪክ ምንነት በአፍሪካም በዓለምም የጎላ የታሪክ ድርሻ ያለው በመሆኑ በተለይ ወጣቱ ትውልድ የአባቶቹን ታሪክ ጠንቅቆ ማወቅና ማክበር ማድመቅ በየወቅቱም መዘከር ይገባዋል። ታሪኩ በአግባቡ ተቀርጾ ከህጻናት ጀምሮ እየተማሩ፣ እያወቁ፣ እያከበሩ እንዲያድጉ ማድረግ ከመንግሥትም ከዜጎችም ይጠበቃል።

የዓድዋ ድል ታሪክ በየትምህርት ቤቱ፣ በየዩኒቨርሲቲው፣ በሁሉም ሥፍራና ቦታ ሁሌም ደምቆና ጎልቶ መታወስ አለበት። ኢትዮጵያን ከጠላት ወራሪ ለመጠበቅና ለመከላከል በዚያ ሩቅ ዘመን ሥልጣኔ ብዙም ባልነበረበት የታሪክ ወቅት አያት ቅድመ አያቶች እንዴት አድርገው ተዋግተው ጠላትን ድል አድርገው አሳፍረው እንደመለሱ እጅግ የላቀና አቻ የሌለው ተጋድሎና የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል ሀገራቸውን እንደጠበቁና እንዳስከበሩ አዲሱ ተተኪ ትውልድ ታሪካቸውን አውቆም ማሳወቅ ይገባዋል። የድሉን መንፈስም ችግሮቹን አሸንፎ ለመውጣት እንደመነሻ ሊጠቀምበት ይገባል።

**« አያት ቅድመ አያቶችና በአርበኝነት ከአራቱም የኢትዮጵያ አቅጣጫዎች ተነስተው ዓድዋ ሲዘምቱ ጉዟቸው በእግር፤ ስንቃቸው በግል ነበር፡፡ የያዙት ስንቅ ቆሎ፣ ዳቦና የቻለው ቋንጣ ነበር። የሚጠጡትም ከአገራቸው ምንጮች የሚያፈልቁትን ውሃ ነበር፡፡ መጠለያቸው የእናት ሀገራቸው ጋራና ሸንተረር ፣ደንና ዋሻ ነበር፡፡ አርበኞች የታጠቁት መሣሪያ ከወራሪው ጣሊያን ጋር ሲመዛዘን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፡፡ እጅግ ኋላ ቀር ነበር»**

ትውልዱ የዛሬውን ነፃነቱን እንዲሁ በቀላሉ አላገኘውም። በየትውልዱ ፈረቃ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ቤዛ ሆነው ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ያስገኙት፣ ያቆዩትና ያስከበሩት ነጻነት ነው። ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ጥንታዊ የመንግሥትነት ታሪክ ከነበራቸው የዓለማችን ጥቂት ሀገሮች ውስጥ አንዷ ናት። በቅኝ ያልተገዛች ብቸኛዋ የአፍሪካ ሀገርም ናት። ይህን ነፃነት ደግሞ የአሁኑ ትውልድ ለምን እንደሚኮራበት መገመት አያዳግትም።

ኢትዮጵያ የብዙ ተፈጥሯዊ ፀጋዎች፣ ታሪካዊ ቅርሶች፣ የውብ መልክዓ ምድርም ባለቤት የሆነች ሀገር ናት። ከውጭ ተስፋፊዎችና ወራሪዎች ሙከራና ትንኮሳ በላይ ታዲያ ሲጎዳት የኖረው ሥልጣኔዋን ወደ ኋላ የጎተተውና ያጫጨው የልጆችዋ እርስ በእርስ መናቆርና እየተጠላለፉ መውደቅ ነው። ለዚህች ታላቅ ሀገርና ጀግና ህዝቧ እንዲህ ዓይነቱ ዝንተ ዓለም ወደ ኋላ ሲጎትት የኖረ አካሄድ አይጠቅምም።

ከጅል ደጅ ሞፈር ይቆረጣል እንዳይሆን ሀገርን አሳልፎ ለውጭ ኃይሎች በር በመክፈት መስጠት የታሪክም የትውልድም ተጠያቂ እንዳያደርግ መጠንቀቅ ይገባል። ከታሪካዊ ስህተቱና ውድቀቱ ያልተማረ ትውልድ ሀገርን አያለማም፤ አያሳድግምም። መናቆርና መባላት ለሀገርም ለሕዝብም አይበጅም። ፖለቲከኞችም መማር ካለባቸው የዚህችን ታላቅ ሀገር በስተኋላ ከክብርዋ የወረደች ዳግማዊ ትንሣዔ የሚሹ ከሆነ ከዓድዋ ድል ብዙ መማር የግድ ይላቸዋል።

በልዩነት ውስጥ ተከባብሮ፣ ተደማምጦና ተቻችሎ መሥራት በጋራ መኖር ሀገርን ማልማትና ማሳደግ ነው። ዓድዋ ላይ በዓለም ፊት ያስመሰከርነውን በአንድነት ውስጥ የሚገለጽ ከአለት የፀና የማይፈረካከስ ጽናት ይዘን ሀገራችንን ጠብቆ ወደፊት መገስገስ ከዚህ ትውልድና ከመጪው ትውልድ ይጠበቃል። የአያት ቅድመ አያቶች እውነተኛ ልጆች መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ አለበት።

ትውልዱ ሥልጡን ሆኖ ልዩነት ውበትም ጥንካሬም መሆኑን አምኖ አንድነቱን ከመቼውም በላይ አጽንቶና አጎልብቶ መራመድ ይኖርበታል። ለኢትዮጵያ ጠላቶች በርና ቀዳዳ ሳይከፍት «ለእኛ ካልሆነች ብትንትንዋ ይውጣ» ከሚሉ የጅል እሳቤዎች መላቀቅ አለበት። መንግሥት ይመጣልም ይሄዳልም፤ ሀገር ግን መተኪያ የሌላት ውድ የተፈጥሮ ስጦታችን ዞሮ መግቢያ እናታችንም ስለሆነች ሠላሟ ተጠብቆ ተከብራና ታፍራ መኖር ለተተኪውም ትውልድ መተላለፍ ያለባት በመሆኑ ፀንተን ልንቆምላት ይገባል።

ከዓድዋ ጦርነትና ድል በመማር ያንን የአባቶችና የአያቶች ፅናት፣ ጀግንነት፣ ብርታትና ወደር የለሽ የመንፈስና የሞራል የበላይነት ትውልዱ ዛሬ ላይ ሆኖ ሀገሩን ለማልማትና ለማሳደግ ሊጠቀምበት ይገባል። የአያት ቅድመ አያት ወኔና ቆራጥነትን በልቡ ውስጥ ማኖር አለበት።

“እናት አባት ቢሞት እህት ወንድም ቢሞት በሀገር ይለቀሳል፤ ሀገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል?” አገሬ አትሙቺ እኔ ልሙትልሽ ብለው ነው በዓድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ ጀግኖች ገድለው እየሞቱም ድል አድርገው የኢትዮጵያን ነጻነት ያስከበሩት። የአሁኑና መጪው ትውልድም ከዓድዋ ብዙ ይማራል ተብሎ ይታሰባል።

# ስፖርት






## የነፃነት ታጋዩ የቦክስ ስፖርት ንጉሥ

**ቦጋስ አበበ**

የምን ጊዜም የቦክስ ስፖርት ንጉሡ መሐመድ አሊ የዓለም የቦክስ ቻምፒዮንና ታላቅ የቡጢ ተፋላሚ ብቻ አልነበረም። የሠብዓዊ መብት ተሟጋች፤ የጥቁር ሕዝቦች ሰንደቅ፤ በመላው ዓለም በስፖርትና በታላቅ ስብዕና ተምሳሌትም ጭምር ነው። ብዙዎች ቦክስ ስፖርት ሳይሆን የጥጋበኞች ድብድብ አድርገው ከመሳል አስተሳሰብ አውጥቶ የቦክስን ስፖርት ጥበባዊ ገፅታ በማላበስ ተወዳጅና አሁን ላይ በዓለማችን በአንድ ጊዜ በርካታ ሚሊዮን ዶላሮች የሚያሳቅፍ ግንባር ቀደምት ስፖርት እንዲሆን ተፅዕኖውን አሳርፏል። ሙዚቀኛም ሆኖ ለሂፕሆፕና ራፕ የሙዚቃ ስልቶች ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

በቦክስ ስፖርት ታሪክ የምንጊዜም ምርጥ ቦክሰኛ የተባለውም በተለያዩ የቡጢ ፍልሚያዎች ዘመን የማይሽራቸው ገድሎችን በማስመዝገብ ነው። መሐመድ አሊ የቦክስ ጓንቱን ሰቅሎ ስፖርቱን በቃኝ ብሎ ከተሰናበተ ከሦስት ዓመታት በኋላ እኤአ በ1984 ከስፖርቱ ልምድ ጋር በተያያዘ ፓርኪንሰንስ በተባለ በሽታ ተይዞ ነበር፡፡ ለሰላሳ ሁለት ዓመታት ከዚህ ህመሙ ጋር ሲታገል ቆይቶ ከአምስት ዓመት በፊት በሰባ አራት ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡

መሐመድ አሊ ወደ ቦክስ ሕይወት የመጣበት አጋጣሚ አስገራሚ ነው። የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ በነበረበት ወቅት ብስክሌቱ ተሰርቆበት በሊውስቪል ኬንታኪ ለሚገኝ ጆ ማርቲን ለተባለ ፖሊስ አመለከተ፡፡ «የሰረቀኝን ባገኘው ልክ አገባው ነበር» ብሎም ምሬቱን ይገልፃል፡፡ የቦክስ አሠልጣኝ የነበረው ፖሊስ ትንሹን መሐመድ ራሱን እንዴት ከጥቃት መከላከል መማር እንዳለበት መከረው። የተወሰኑ ሥልጠናዎችን ሲወስድ ቆይቶም ብስክሌቱ ከተሰረቀች ከስድስት ሳምንታት በኋላ በሰፈሩ በአንድ አማተር የቦክስ ግጥሚያ ላይ ተሳተፈና በነጥብ አሸናፊ መሆን ቻለ፡፡ ይህች አጋጣሚም በዓለም ለገነነበት ስፖርት የመሠረት ድንጋይ ነች።



መሐመድ የትውልድ ስሙ ካሴስ ክሌይ ቢሆንም በ19ኛው ክፍለ ዘመን ባሮችን ነፃ ለማውጣት በታገሉ ታላቅ ሰው መታሰቢያነት የወጣለት ስም ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም ከባድ ሚዛን ቻምፒዮን ከሆነ በኋላ በማግስቱ ስሙን ለመቀየር ወሰነ፡፡ የነፃነት ታጋዩን ማልኮለም ኤክስ ከጎኑ አድርጎ በሰጠው መግለጫ «ዘ ኔሽን ኦፍ ኢስላም» የተባለውን ተቋም መቀላቀሉን በማሳወቅ የባርያ ስም ይለው የነበረውን ካሴስ ክሌይ በመቀየር በቀድሞ ስሙ ላለመጠራት ወሰነ። በወቅቱ «ኔሽን ኦፍ ኢስላምን» ይመራ የነበረው ኤልጅያህ መሃመድ እኤአ በ1964 ላይ መሐመድ አሊ የሚለውን ስም ካወጣለት በኋላ እሱን በማፅደቅ እስከ ሕይወት ዘመኑ መጨረሻ ተጠራበት።

ለሃያ አንድ ዓመታት በፕሮፌሽናል ቦክሰኛነት በርካታ የቡጢ ፍልሚያዎችን ከአሜሪካ እስከ አፍሪካ እንዲሁም ሌሎች ዓለማት ላይ የተፋለመው መሐመድ አሊ ለሦስት ጊዜ የዓለም ከባድ ሚዛን ቻምፒዮን ሆኗል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም የከባድ ሚዛን ሻምፒዮን ለመሆን የበቃውም የሃያ ሁለት ዓመት ወጣት እያለ ነው። ዓለም አቀፍ ደረጃ ባላቸው ፕሮፌሽናል የቦክስ ግጥሚያዎች ላይ ስልሳ አንድ ጊዜ ተሳትፎ ሃምሳ ስድስቱን ማሸነፍም ችሏል። ከእነዚህ ድሎቹም ሰላሳ ሰባት ያህሉን ተጋጣሚዎቹን በበቃኝ በመዘረር ነው። አስገራሚው ነገር በሰላሳ አንድ ተከታታይ የቦክስ ግጥሚያዎች ሳይሸነፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸነፈው የክፍለ ዘመኑ ምርጥ ፍልሚያ በተባለው ግጥሚያ በጆ ፍሬዘር ነበር። በፕሮፌሽናል የቦክሰኛነት ዘመኑም ሽንፈትን የቀመሰው አምስት ጊዜ ብቻ ነው።

የመጨረሻውን ፍልሚያም እኤአ በ1981 ከትሬቨር ቤሪቢክ ጋር በማድረግ ስፖርቱን በቃኝ ብሏል። አሜሪካ በቬትናም በ1970ዎቹ መጀመሪያ ያደረገችውን ጦርነት በመቃወሙ ለሦስት ዓመታት ከፕሮፌሽናል ቦክስ ውድድሮች ታግዶ የቆየው መሐመድ አሊ እገዳው በተጣለበት ወቅት ከአስር የማያንሱ የዓለም ከባድ ሚዛን ቻምፒዮናዎች ባያመልጡት አሁን ካሉት የበለጠ በርካታ ክብሮችን መጎናፀፍ ይችል ነበር። በዚህም ከሰማንያ ሚሊዮን ዶላር በላይ ሀብት ማፍራት ችሏል። ለዚህ ሀብቱም ምንጭ ስፖርቱን ከተሰናበተ ወዲህ ግንባር ቀደም ተዋናዮቹ ስሙንና ምስሉን የሚጠቀሙ ከአርባ በላይ ኩባንያዎች ናቸው። ታሪካዊው ኢትዮጵያዊ አትሌት አበበ ቢቂላ በ1960 የሮም ኦሊምፒክ በባዶ እግሩ ሮጦ ለጥቁር ሕዝቦች የመጀመሪያውን የማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ሲያስመዘግብ መሐመድ አሊም በቦክስ የወርቅ ሜዳሊያ አጥልቆ ነበር። ሁለቱ ታሪካዊ የጥቁር ሕዝቦች ከዋክብት ፊርማቸውን ተለዋውጠውም ነበር። ይሁንና መሐመድ አሊ ይህን የወርቅ ሜዳልያውን ለሀገሩ ከማበርከት ይልቅ በሊውስ ቪል ግዛት በሚገኘው የኦሃዮ ወንዝ ጨምሮታል። ሜዳልያውን ለአሜሪካና ለትውልድ ከተማው ሊውስ ቪል ቢቀዳጅም በርገር የመግዛት መብት ባለመኖሩ ተቃውሞውን ለመግለፅ ነበር ይህን ርምጃ የወሰደው።

በ1996 ሀገሩ አሜሪካ ባስተናገደችው የአትላንታ ኦሊምፒክ ችቦውን እንዲለኩስ ከመደረጉ ባሻገር ወንዝ የጨመረው የወርቅ ሜዳልያ ምትክ ሌላ ሜዳሊያ በአንገቱ ተጠልቆለታል። በ1980 በላስቬጋስ በተካሄደ የቡጢ ፍልሚያ በቴክኒካል የበቃኝ ውጤት ቢሸነፍም መሐመድ ትልቁን ክፍያ ስምንት ሚሊዮን ዶላር ያፈሰው በዚያ ውድድር ነው። «ራምብል ኢን ዘ ጃንግል» በተባለውና እስካሁንም ከስፖርት ቤተሰቡ አዕምሮ በማይጠፋው በአፍሪካ ምድር በተካሄደው ፍልሚያ መሐመድ አሊ ምን ጊዜም ይታወሳል።

እኤአ በ1974 መሐመድ አሊ በሰላሳ ሁለት ዓመቱ ሽንፈትን አይቶ ከማያውቀው ከሃያ አምስት ዓመቱ ጆርጅ ፎርማን ጋር በኮንጎ ኪንሻሳ የቡጢ ፍልሚያ ገጥሞ ነበር። በወቅቱ የኮንጎ ፕሬዚዳንት የነበሩት ሞቡቱ ሴሴሴኮ ለሁለቱ ቦክሰኞች በኪንሻሳ ከተማ እንዲጫወቱ በነፍስ ወከፍ አምስት ሚሊዮን ዶላር ከፍሏቸው ነበር፡፡

መሐመድ አሊ በውድድሩ ስምንተኛ ዙር ላይ በዝረራ ቢሸነፍም ከወጣት ተፋላሚው ጋር ያደረገው እልህ አስጨራሽ የቡጢ ፍልሚያ እስካሁንም ከህሊና የሚጠፋ አይደለም። በ1970 የዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ መታሰቢያ ሽልማት የተቀበለው መሐመድ አሊ፤ የዓለም አቀፋዊ ወዳጅነት ተምሳሌት ሆኖም ያውቃል። የተባበሩት መንግሥታት የሰላም መልዕክተኛ ሆኖም ከ1998 እስከ 2008 በታዳጊ ሀገራት በመዘዋወር አገልግሏል። በሕይወቱ ዙሪያ በሚያተኩሩ ጥናታዊና የሙሉ ጊዜ ፊልሞች የሠራ ሲሆን በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀውና ዘ ግሬተስት በተባለ ፊልም ላይ ተውኗል፡፡ የሕይወት ታሪኩ ላይ በማተኮር ከተሠሩ ፊልሞች የኦስካር ሽልማት በጥናታዊ ፊልም ዘርፍ ያገኘው «ዌን ዊ ዌር ኪንግስ»ና ዝነኛው የሆሊውድ ተዋናይ ዊል ስሚዝ በመሪ ተዋናይነት የተጫወተው «አሊ» የተባሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ታላቁን የደቡብ አፍሪካ ነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ ከእስር እንደተፈቱ በአካል ተገኝቶ ደስታውን ለመግለፅ መሐመድን የቀደመው የለም። በአካል ካገኛቸው ታላላቅ መሪዎች የእንግሊዟ ንግሥት ኤልሳቤጥ፤ የሮማው ሊቃነ ጳጳስ ፖፕ ጆን ፖል፤ የኩባው መሪ ፊደል ካስትሮ እንዲሁም የኢራቁ ሳዳም ሁሴን ይገኙበታል፡፡




## ከዓድዋ ድል ምን እንማራለን?

**እዮሩስ ተስፋዬ**

ሠላም ልጆችዬ እንዴት ናችሁ? ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ትምህርታችሁ ላይ እየበረታችሁ ነው አይደል? በጣም ጎበዞች፡፡ መቼም ቅዳሜ እና እሁድ ለእናንተ የተወሰነ እረፍት የምታገኙበት ቀናት ናቸው፡፡ ታዲያ በነዚህ ቀናት እያጠናችሁ፣ ጋዜጣ፣ መጻሕፍትን እያነበባችሁ እንዲሁም በጥቂቱም ቢሆን እየተጫወታችሁ እንደምታሳልፉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡




ልጆችዬ ለዛሬ ወደ ምናቀርብላችሁ ርዕሰ ጉዳይ ከመግባታችን በፊት እስቲ እንኳን አደረሳችሁ? እንባባል፡፡ መቼም ‹‹ለምኑ?›› እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ትናንት የካቲት 23 ቀን 2016 ዓ.ም 128ኛው የዓድዋ ድል በድምቀት እንደተከበረ ታውቃላችሁ፡፡ ለዛ ነው እንኳን አደረሳችሁ ያልናችሁ፡፡ ይህ ቀን ለሁሉም ኢትዮጵያውን የተለየ ነው አይደል? ‹‹በሚገባ!›› ምክንያቱም አብዛኛው የአውሮፓ ሀገራት (ነጮች) አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለመቆጣጠር ያደረጉት ጥረት የከሸፈበት ስለነበር፡፡ የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን በቁጥጥሩ ሥር አውሎ በቅኝ ለመገግዛት ያደረገው ጥረት የከሸፈበት ቀን በመሆኑ የተለየ ነው፡፡

ልጆችዬ በየካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በዓድዋ ተራራማ አካባቢዎች በኢትዮጵያ እና በጣሊያን ቅኝ ገዥ ጦር መካከል ጦርነት መካሄዱ ይታወቃል፡፡ አንድ ቀን በፈጀው ጦርነት የጣሊያን ጦር በኢትዮጵያ ተሸንፏል። ይህንን የድል በዓል በማሰብ በተለያዩ መንገዶች ሲከበር እንደተመለከታችሁ ጥርጥር የለኝም፡፡

በዓድዋ ድል ሁሉም ሰው እኩል እንደሆነ ማሳየት ተችሏል፡፡ በቅኝ አገዛዝ ለነበሩት የአፍሪካ ሀገራትም ኢትዮጵያ ምሳሌ ሆና ብዙዎች ከቅኝ አገዛዝ እንዲወጡ መነሳሳትን ፈጥራለች፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩት ዳግማዊ አፄ ምንሊክ እና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ጦርነቱን በመምራት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። በተጨማሪም ከአራቱም አቅጣጫ ከደቡብ፣ ከምስራቅ፣ ከሰሜን እና ከደቡቡ የሀገራችን ክፍል የተውጣጡ ጀግኖች ሀገራችን በነፃነቷ እንድትቀጥል እስከሞት ድረስ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡

ልጆችዬ ጣሊያንን ለማሸነፍ ብዙ ዋጋ እንደተከፈለ ተረዳችሁ አይደል ? ስለዚህም ወራሪ የነበረው የጣሊያን ጦር ከሁሉም የሀገራችን ክፍሎች በተውጣጡ ጀግኖች ለማሸነፍ ተችሏል፡፡ በወቅቱ ጣሊያን ከኢትዮጵያ የምትበልጥ ሀገር ብትሆንም እኛ ኢትዮጵያውያን ግን በአንድነት እና በሕብረት ሆነን የማይቻል የሚመስል ነገር አድርገናል፡፡ ልጆችዬ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው ማንንም መናቅ እንደማይገባ ነው፡፡ በአፍሪካ ደረጃ ይህን ያደረገ ሀገር እንደሌለስ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ ‹‹አዎ በሚገባ ከአፍሪካ ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ ናት!›› እንደምትሉ እተማመናለሁ፡፡

ልጆችዬ ሀገራችን ኢትዮጵያ በነፃነቷ ድርድር የማታውቅ ሀገር እንደሆነች ተገንዝባችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በተጨማሪም የአኩሪ ድል ባለቤት ሀገር እንደሆነችም ታውቃላችሁ፡፡ ለዚህ እኮ ነው ልጆችዬ ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ታሪክ፣ ባህል፣ እሴት እና የደማቅ ድል ባለቤት እንደሆነች በኩራት የምንነግራችሁ፡፡

ዛሬ እናተን እና እኛ ያለምንም የውጭ ሀገር ተጽዕኖ በነጻነት እንድንኖር የቀደሙት ጀግኖች አባቶቻችን እና እናቶቻችን ብዙ ዋጋ ከፍለውበታል፡፡ ልጆችዬ ሁሉም የሰው ልጆች እኩል እንደሆኑ ታወቃላችሁ አይደል? ነጭ፣ ጥቁር፣ ደሃ፣ ሀብታም እና የመሳሰሉት ስያሜዎች በመስጠት ይኑሩ እንጂ ሁሉም የሰው ልጅ እኩል ነው፡፡ ታዲያ በዛ ዘመን የነበሩ የአውሮፓ ሀገራት ራሳቸውን የበላይ አድርገው ነበር የሚቆጥሩት፡፡ እኛን ጥቁር አፍሪካውያንን ደግሞ የበታች አድርገው ነበር የሚመለከቱን፡፡ እኛ አፍሪካውያንን ባሪያ እና ተገዢ ለማድረግ ጥረት ቢያደርጉም ግን በዓድዋ ምክንያት አልተሳካላቸውም፡፡ ለዚህም ነው ‹‹ዓድዋ የሁሉም ጥቁር ሕዝብ ድል እና ኩራት ነው፡፡›› የሚባለው፡፡

ልጆችዬ እናንተም ስለ ዓድዋም ይሁን ስለአገራችሁ ታሪክ ለማወቅ ወላጆቻችሁ፣ መምህራን እና ታላላቆቻችሁን ብትጠይቁ እንደሚነግሯችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እናነተም ከወላጆቻችሁ እና ከመምህራን ያወቃችሁትን አኩሪ ታሪክ ላላወቁት በመንገር ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር ማስተማር ይገባችኋል፡፡

እናም ልጆችዬ ከዓድዋ ድል ብዙ ነገሮች እንደተማራችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ ‹‹ምን ተማራችሁ?›› ተብላችሁ ብትጠየቁ እንኳን መተባበርን፣ ፍቅርን፣ አንድነትን ለመጥፎ ነገር አለመተባበር፣ ጀግንነት፣ አሸናፊነትም እና ሌሎችን ተምረንበታል ብላችሁ ምላሽ እንደምትሰጡን አልጠራጠርም፡፡ ሌላው ደግሞ ማንም የራሱ ያልሆነውን ነገር መፈለግ እና መሻት እንደሌለበት በሚገባ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ልጆችዬ ዛሬ ታላቁን የዓድዋ የድል በዓል ምክንያት በማድረግ ስለ ድሉ በጥቂቱም ቢሆን አቀረብንላችሁ፡፡ ሳምንት በሌላ ርዕሰ ጉዳይ እንደምንገናኝ ተስፋ በማድረግ ለዛሬው በዚሁ እንስነባበታለን፡፡ ሳምንት በቸር ያገናኘን፡፡